አዲስ ዘመን
ኢፕድ
እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 183 መጋቢት 3 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ምርትን በመያዝ

## ስፖለቲካ መጠቀሚያ በሚያደርጉ ላይ ቁጥጥር ይደረጋል

- የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል
- የጤፍ ዋጋ ዝቅ እንዲል እንሠራለን


ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

አቶ ጃንጥራር ዓባይ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ምርትን በመያዝ ለሌላ የፖለቲካ ቀውስ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚደረጉ ሙከራዎች ላይ መንግሥት ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚያደርግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ። የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ግብረ-ኃይል ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱንና የጤፍ ዋጋ ከተጋነነው ጭማሪ ዝቅ እንደሚሠራ ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ከወቅታዊው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከጥር ወር አጋማሽ በኋላ ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር በሕገ ወጥ መንገድ

ምርትን በመያዝ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# በሶማሌ ክልል ለድርቅ ተጎጂዎች ሰብዓዊ ድጋፍ እየቀረበ ነው

- 4 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተረጂዎች ተለይተዋል

**ጸጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል ለሚገኙ የድርቅ ተጎጂዎች የዓለም ምግብ ፕሮግራም ድጋፍ እያቀረበ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ገለጸ።

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በክልሉ ከሚገኙ 11 ዞኖች መካከል ዘጠኙ ዞኖች በድርቅ የተጠቁ

በሶማሌ ክልል ለድርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ሰብዓዊ ዕርዳታ በሸረ ከተማ

ገጽ 4

# ባጃጅ ተሽከርካሪዎች በቅርቡ ወደ ስራቸው ይመለሳሉ


አቶ ምትኩ አስማረ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ባጃጅ ተሽከርካሪዎች በቅርቡ ወደ መደበኛ ስራቸው እንደሚመለሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ምትኩ አስማረ በቅርቡ በመዲናዋ እየተነሳ ካለው የባጃጅ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ የከተማ አስተዳደሩ የባጃጅ አገልግሎትን የተሻለ ለማድረግ የአሰራር ማስተካከያ እያደረገ ነው። ይህ እስከሚጠናቀቅ ድረስም የባጃጅ አሽከርካሪዎችና ተጠቃሚዎች በትዕግስት እንዲጠብቁ አሳስበዋል።

የትራንስፖርት ሥርዓቱን ለማዘመን የተለያዩ

ባጃጅ ተሽከርካሪዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







አቶ ገብረ መስቀል ጫላ

## የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን የሚመጥን የአሰራር መዋቅር ሊኖር ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን የሚመጥን ጠንካራ የአሰራር መዋቅርና ዕድሉን የሚጠቀም የግሉ ሴክተር ሊኖር እንደሚገባ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረ መስቀል ጫላ አስገነዘቡ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ማሻሻያ ረቂቅ ዙሪያ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰራተኞችን፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን ሰብስቦ በትናንትናው እለት አወያይቷል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር አቶ ገብረ መስቀል ጫላ በውይይቱ እንደተናገሩት፤ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን የሚመጥን ጠንካራ የአሰራር መዋቅርና የግል ዘርፍ ሊኖር ይገባል። ለዚህም የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን ለመቀረፍ አዲስ የማሻሻያ አዋጅ ተዘጋጅቷል። ለዚህም አስፈላጊውን ግብዓት ለማግኘት ሲባል ይህ የውይይት መድረክ ተዘጋጅቷል።

አዋጁ ለ20 ዓመታት በመቆየቱ የዓለምን ተለዋዋጭ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ማሻሻያ ማድረግ አስፈልጓል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የተደረገው ማሻሻያ አምራቹን፣ ነጋዴውንና ሸማቹን ያቀፈ የንግድ ሥርዓት ለመፍጠር አስተዋጽኦው የጎላ ነው። በውይይት መድረኩም የተነሱት ሃሳቦች ማሻሻያ አዋጁን የሚያዳብሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

አዋጁ የግሉን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ በቡድን ጠንካራ አደረጃጀት ለመፍጠር ይረዳል ያሉት ሚኒስትር አቶ ገብረ መስቀል፤ የግሉን ዘርፍ ይበልጥ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ እና ሀገራዊ እድገትን ለማፋጠን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በርካታ ስራዎች እየተሰራ ነው ብለዋል።

በንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር የላይሰንሲንግና ሬጉላቶሪ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጅራታ ነመራ ስለማሻሻያ አዋጁ እንዳብራሩት፤ ለ20 ዓመታት የቆየው አዋጅ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ብሎ ሲደነገግ ዘርፉ ምን እንደሆነ በቅጡ አላብራራም። ከዚህም ባለፈ አዋጁ በአምራቹ ዘርፍ ያሉትን ማህበራት ለመደገፍ ታስቦ የተዘጋጀ ነው ይባላል። ነገር ግን በዘርፍ መደራጀት ያለባቸው ሌሎች ዘርፎችን የሚያቅፍ አይደለም።

የተሻሻለው አዋጅ ግን ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ነው። አዋጁ ያላካተታቸው እና መካተት ያለባቸው ጉዳዮች አሉ የሚሉ አካላት ጉዳዮችን በጽሁፍ እንዲያመጡ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይጠይቃል ብለዋል።

የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሰብስብ አባፍራው በበኩላቸው፤ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/1995 የግሉን ዘርፍ አንድነት ያዳከመ ነው። በአንጻሩ ማሻሻያ አዋጁ የግሉን ዘርፍ አንድነት የሚያጠናክር እና በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ፋሲካው ሲሳይ በውይይቱ እንደተናገሩት፤ ማሻሻያ የአዋጁ የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚያስችል ነው። ነገር ግን የአምራቹን ዘርፍ ችግሮች የሚፈታ መሆን አለበት። ማሻሻያ አዋጁ የአምራቹን ዘርፉ የአደረጃጀት አካል ሆኖ በመመሪያ መቀመጥ አለበት። እንደ አዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአምራች ዘርፉ ችግር በውስጥ ደንብ ይፈታል ብለን አናምንም። እናም ከአዋጁ በተጓዳኝ ግልጽ የሆነ መመሪያ ሊኖር ይገባል ።

# በደቡብ ኦሞ ዞን 2 ነጥብ 3 ሚሊዮን እንስሳት ለመኖና ውሃ እጥረት ተጋልጠዋል

### - ለ338 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ እየተደረገ ነው

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን በተከሰተው ድርቅ ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ እንስሳት ለመኖና ውሃ እጥረት መጋለጣቸውን የደቡብ ኦሞ ዞን አስታወቀ። በተከሰተው ድርቅ ተጎጂ ለሆኑ 337 ሺህ 923 በላይ ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ንጋቱ ዳንሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ በተለይ ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች ባለፉት ሦስት ዓመታት የዝናብ እጥረት በመኖሩ ድርቅ ተከስቷል።

በዞኑ በደረሰው ድርቅ የውሃና የመኖ እጥረት በመከሰቱ ከሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ እንስሳት ለመኖና ውሃ እጥረት ተጋልጠዋል። የምግብ ድጋፍ ፈላጊዎች ቁጥርም 420 ሺህ 447 ደርሷል ብለዋል።

በእስካሁ ጥረት ለ337 ሺህ 923 ሕዝብ ለአስቸኳይ ምግብ ዕርዳታ ድጋፍ ማቅረብ እንደተቻለ ገልጸው፤ ድርቁ ያደረሰውን ጉዳት ለመከላከል በደቡብ ክልልና በፌዴራል መንግሥት በኩል የተለያዩ የሰብዓዊ ድጋፎች እየቀረቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ድርቁ ከዚህም በላይ ሳይከፋ በርካታ እንስሳት ሳር ወዳለባቸው አካባቢዎች እንዲንቀሳቀሱ በተለይም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሱርማ አካባቢ በሚገኙ ቦታዎች እንዲጓጓዙ እንዲሁም ቁርካና ሐይቅ አካባቢ ባለው ውሃ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ለማድረግ ሙከራ መደረጉን ዋና አስተዳዳሪው አንስተዋል።

በዞኑ ለሰውና እንስሳት ውሃ የሚያቀርቡ 15 ቦቴዎች እንዲሰማሩ በደቡብ ክልል መንግሥት ተወስኖ በሂደት ላይ ነው፤ እስካሁንም ሶስት ቦቴዎች ወደ ዞኑ ደርሰው የከፋ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ድጋፍ እያደረጉ ነው ብለዋል።

ብሔራዊ የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ድጋፉን በማስተባበር ላይ ይገኛል። በወርልድ ቪዥን በኩልም ባለፉት ሁለት ወራት የጥራጥሬ እህልና ዘይት ድጋፍ ተደርጓል። የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ ድርጅት 450 ኩንታል የበቆሎ ዱቄት መላኩንም አቶ ንጋቱ ጠቁመዋል።

የደቡብ ኦሞ ዞን አርሶአደሮችን እንዲሁም አጎራባች ዞንና በኬንያ ድንበር የሚገኙ አርብቶ አደሮችን ጭምር ያስጠቅም የነበረው ወይጦ ወንዝ በድርቁ ምክንያት ሙሉ በሙሉ በመድረቁ እንስሳትና ሰዎች ለችግር መጋለጣቸውን አስረድተዋል።

አቶ ንጋቱ እንዳስታወቁት፤ በደቡብ ኦሞ ዞን ከፊል አርብቶ አደር በሆኑት ዳሰነች፣ ማሌ፣ ሐመር፣ ኛንጋቶም፣ በናፀማይ እና ሳላማጎ ወረዳዎች ባለፈው መኸር ወቅት ዝናብ ባለመኖሩ ምርት ማምረት አልተቻለም የበልግ ወር ከገባ ጀምሮም እስካሁን ዝናብ ባለመዝነቡ የድርቁን ጉዳት ከፍተኛ አድርጎታል።

ከእንስሳት የድርቅ ተጋላጭነት አንፃር ሐመር ወረዳ ከፍተኛ ችግር አለ። በተጨማሪ በዞኑ በባለሀብቶች የተያዙ 5 ሺህ ሄክታር የእርሻ ኢንቨስትመንቶች እንዲሁም የተለያዩ አትክልት እና ፍራፍሬዎች ልማት ስራዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ የውሃ እጥረቱ እንቅፋት ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመት 700 ሺህ እንስሳት ለአደጋ ተጋልጠው እንደነበር አስታውሰው በሰብል ተረፈ ምርት እና በተለያዩ አማራጮች በመመገብ የእንስሳቱን ሕይወት ለማቆየት ተሞክሯል ብለዋል።

ተከታታይነት ያለው ድርቅ በዳሰነች፣ ሐመርና ኛንጋቶም ወረዳዎች ላይ ተከታታይ ችግር በመከሰቱ መንግሥት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ብቻ ለ282 ሺህ ያህል ዜጎች በሴፍቲኔት መርሃ ግብር ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰዋል።

በችግሩ ምክንያት የምግብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው እናቶችና ህፃናት አስፈላጊውን ሰብዓዊነት ድጋፍ ለማቅረብ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ተቋማት እንዲሁም ግለሰቦች እንዲተባበሩ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ጥሪ አቅርበዋል።

# ጃፓን በጦርነትና በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁነቷን አስታወቀች

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- ጃፓን በኢትዮጵያ በጦርነት እና በድርቅ ምክንያት ለደረሱ ጉዳቶች ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ተካኮ አስታወቁ።

በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጃፓን ከዚህ ቀደም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው አማራ፣ አፋር እና ትግራይ ክልሎች አስቸኳይ ሰብዓዊ ዕርዳታ ስትሰጥ ቆይታለች።

በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል ተጎድተው የነበሩ መሰረተ ልማቶችን መልሶ ግንባታ ማድረግ ከባድ ሥራ ነው ያሉት አምባሳደሯ፤ በዚህም ምክንያት ለተጎዱት ፕሮጀክቶች ምን ያህል የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ መንግሥት ካሳወቀን የጃፓን መንግሥት ለማገዝ ዝግጁ ነው ሲሉ ገልጸዋል።


አምባሳደር ኢቶ ተካኮ

ከዚህ ቀደም በድርቅ እና በግጭት ለተጎዱ ዜጎች ያለማቋረጥ ሰብዓዊ ድጋፍ ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመውም፤ የደቡባዊ ምሥራቅ ክልሎች ከፍተኛ ድርቅ ስላጋጠማቸው አስቸኳይ ዕርዳታ በሌሎች ድርጅቶች በኩል ሲደግፉ መቆየታቸውን አብራርተዋል።

የሰብዓዊ ዕርዳታውን እያደረግን የድርቁን ተጽዕኖው ለመከላከል እና ለመቀነስ ተጋግዘን ብዙ መስራት አለብን ያሉት አምባሳደር ኢቶ፤ ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የመስኖ ልማት የግብርና ሥራዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በትብብር ለመሥራት ዝግጁነታቸውንም አመላክተዋል።

እንደ አምባሳደሯ ገለጻ፤ የጃፓን ባለሀብቶች ወደ አፍሪካ ለመምጣት ፍላጎት አላቸው፤ መዋዕለ ነዋያቸውን ለማፍሰስ ከሚፈልጉባቸው አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ሆኖም የልማት ፍላጎቱን ለማረጋገጥ የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት ማስፈን ባለሀብቶቹን ለመሳብ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

“በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው ትብብራችን በሰብዓዊ ዕርዳታ ላይ ያተኮረ ነው፤ ነገር ግን ትብብራችንን በስፋት እና በመጠን ሰፊ ማድረግ እንችላለን” ሲሉም አክለው ገልጸዋል። ከኢትዮጵያ ጋርም የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል፣ የምግብ እህሎችን ምርታማነት ለማሳደግ እንዲሁም የሴቶች እና ህጻናት ጉዳይ ላይ በጋራ ልንሠራ የምንችልባቸው ብዙ ዕድሎች እና እምቅ አቅሞችም አሉን ነው ያሉት።

በኢትዮጵያ የሚደረገውን ሀገራዊ የምክክር ሂደት እንደሚደግፉ ያስታወቁት አምባሳደሯ፤ ሂደቱን ለመደገፍ ጃፓን ቁርጠኝነት አላት ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ፈተናዎችን በጽናትና በአንድነት እንመክት!

ኢትዮጵያ በለውጥ ምህዋር ላይ ትገኛለች። ይህ ለውጥ ብዙ መልካም ነገሮችና ስኬቶች እንዳሉት ሁሉ ፈተናዎችም አሉበት። እነዚህን ፈተናዎች በትዕግስት፣ በጽናትና በአንድነት እያለፉ መልካም ነገሮችና ስኬቶችን ይዞ ወደፊት መጓዝ የግድ ይላል።

በመጪው መጋቢት 24 ቀን 2015 ዓ.ም አምስተኛ አመቱን የሚደፍነው የሀገራችን የለውጥ ጉዞ በበርካታ ድሎች የታጀበ ነው። ታላላቅ ፕሮጀክቶች ተጀምረው የተጠናቀቁበት፣ አደጋ ላይ የነበሩ እንደ ህዳሴ ግድብ ያሉ ፕሮጀክቶችም ከችግራቸው ወጥተው በስኬት ተጉዘው ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት የጀመሩበት የለውጥና የድል ዘመን ነው።

በግንባታ ሂደት ያሉት የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች እንዲሁም ተጠናቀው ስራ የጀመሩት የወዳጅነት ፓርክ፣ የአንድነት ፓርክ የሳይንስ ሙዝየም እና ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶች የለውጡ ቱሩፋቶች ናቸው። በሀገር በቀል የኢኮኖሚ መርሃ ግብርም እነዚህን የለውጥ ትሩፋቶች ላይ ተጨማሪ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችሉ ሥራዎች በግብርና፣ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ ተሰርተዋል፤ እየተሰሩም ነው።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚን ለመገንባትም ዘላቂነት ያለው የ 10 ዓመታት የኢኮኖሚ ዕቅድ ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። ዕቅዱ በግሉ ዘርፍ የሚመራ፣ ተወዳዳሪ፣ ሀብት ቆጣቢ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ሽግግርን በማሳለጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትን ለማስፈን ያለመ ነው።

በሀገር በቀሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብርም በዘላቂ ዕድገት መርሆዎች የተደገፈ በመሆኑ፤ ለግብርና፣ ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለቱሪዝም፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ምሰሶዎች ቅድሚያ ይሰጣል።

በታዳሽ ኃይል ልማት ዘርፍም ከውሃ፣ ከነፋስ፣ ከጸሃይ እና ከእንፋሎት ሃይል በማመንጨት እና እነዚህን እምቅ ሀብቶች መሰረት በማድረግ እአአ 2050 የካርበን ልቀትን ዜሮ ለማድረስ ትኩረት በመስጠት እየተሰራ ነው።

በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርም ለተከታታይ አራት ዓመታት 25 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። ይኸው ስኬት 64 ሚሊዮን በጋዝ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ለአንድ ዓመት ወደ ከባቢ አየር የሚለቁትን የተበከለ አየር የሚያስቀር ነው።

ይህ ውጤት የተገኘው ባለፉት አራት ዓመታት የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ 25 ሚሊዮን ዜጎች ችግኞችን በማፍላት፣ የችግኝ ጉድጓድ በመቆፈር፣ በመትከል በመንከባከብ በመሳተፋቸው ነው። በውጤቱም 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ በአፈፃፀም ግን 25 ቢሊዮን ችግኝ ተተክለዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻው ሲጀመር 40 ሺህ ብቻ የነበሩት የችግኝ ማፍያዎች አሁን ላይ ወደ 121 ሺህ አድገዋል። በዓመት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ የማፍላት አቅም ላይ ደርሰዋል። አረንጓዴ ባህልን ከመፍጠር ባለፈ ዘመቻው ለ767 ሺህ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ያበረከተው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦም ቀላል አይደለም።

በግብርና ልማትም በተለይ በፍራፍሬና ስንዴ ልማት፤ በበጋ መስኖ በተሰሩ ስራዎች የስንዴን ወጪ ንግድ ማድረግ የሚያስችል አቅም ተፈጥሯል። በሌሎችም ዘርፎች ተመሳሳይ ድሎችና እድሎች አሉ። ይህን መልካም ስራ፣ ድልና እድል አሟጦ በመጠቀም የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ደግሞ በትዕግስት፣ በፅናትና በአንድነት በማለፍ የብልጽግና ጉዞን የተቃና ማድረግ ያስፈልጋል።

ከላይ የተዘረዘሩትም ሆነ ያልተገለፁት ስኬቶች፣ ድሎችና ዕድሎች ቢኖሩም በአንፃሩ ደግሞ ፈተናዎች አሉ። ከእነዚህ ፈተናዎች አንዱ ከፀጥታና ደህንነት ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመው ነው። ይህ ፈተና የሚመነጨው ካልዳበረ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ባህል እንዲሁም የተቋማት ግንባታ ጠንካራና ዘላቂነት ያለው አለመሆን ነው።

የሃሳብ ልዩነት በውይይትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍታት ሲገባ፤ ሥልጣንም በምርጫ መያዝ የግድ ሆኖ እያለ፣ የሚሸጥ ሃሳብ ይዞ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ጥረት ማድረግ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሁሁ መሆኑ እየታወቀ፤ ይህን ወደ ጎን በመተው በግጭት ለማትረፍ የሚፈልጉ ኃይሎች የብልጽግና ጉዞው፣ ድሎቹና ዕድሎቹ ላይ ፈተናዎች በመሆናቸው በጽናት ታግሎ ማለፍ ይገባል። ሕዝብም ሆነ ሀገር ከሰላም እንጂ ከግጭት ማትረፍ እንደማይችል ለሁለት ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ ከነበረው ጦርነት ተምሮ የግጭት ነጋዴዎች በአንድነት በቃችሁ ሊላቸው የግድ ነው።

ከዋጋ ንረትና ኑሮ ውድነት ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ፈተናዎችም በተለይ ሰው ሰራሽ የሆኑትን የንግድ ሥርዓቱ ዘመናዊ በማድረግና ምርትና ምርታማነት በማሳደግ መፍታት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ብቻውን ሳይሆን ኅብረተሰቡንም ባሳተፈ መልኩ መስራት የግድ ይላል። በመልካም አስተዳደር ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮችንም የአሰራር ሥርዓት በማዘመን መልካም አገልግሎት በመስጠት ማስተካከል ይገባል።

በአጠቃላይ መፃኢ የሀገራችን እድል ከፈተና ይልቅ ተስፋ ድልና ዕድሎች የሚበዙበት ነው። ስለሆነም ሁሉንም ችግሮችና ፈተናዎች ከእኛ ጥንካሬ በታች መሆናቸውን አውቀን በፅናትና በአንድነት ታግለንና ሰርተን ማሸነፍ አለብን!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## በዓድዋው የድል መንፈስ የአዲስ ታሪክ ባለቤት ለመሆን

በእምነት

አፍሪካን ልክ እንደ ቅርጫ ስጋ በመበጣጠስና በመቆራረጥ በሚመቻቸው መጠን ማሳነስና ባሪያ አድርጎ ማስቀጠል የአውሮፓውያኑ የወቅቱ ህልም ነበር ። የወቅቱ ሀሳብ አመንጪ ፖርቹጋል ብትሆንም አውሮፓውያን በሁሉም አጋጣሚ አፍሪካን ለመበዝበዝ ተዘጋጅተው ነበር ።

በአውሮፓውያን የቅርጫው ድርድር (ክፍፍል) ሲወጣ እድለ ቢሷ ጣሊያን ከወደ ምስራቅ አፍሪካ የሆነችውን በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገችው "ኢትዮጵያ" የምትባል አገር ደረሳት። አንዳንድ እጣ አነሳስ ወደ መቃብር ሊያመራ እንደሚችል አላወቀችምና ጣሊያን የደረሳትን ድርሻ በፈገግታ ነበር የተቀበለችው።

ያልተነካ የተፈጥሮ ሀብትን ነፋሻማ አየሯን የለመለመች ምድርን ለመቀራመት ባሰበችበት ሰዓትም ልቧ በደስታ ዘለለች፤ ወደ ማዕበል እሳት እየተጓዘች ስለመሆኑ ግን ምንም አልጠረጠረችም።

ታዲያ ትልቅ ምኞት ደስታና ሀብት ሰንቃ አይኗን በጨው ታጥባ ጉዞዋን ወደ ኢትዮጵያ ያደረገችው ጣሊያን በኃይልና በማደናገር ብርቅየዋን አገር ለመቆጣጠር እቅድ ነድፋ ተንቀሳቀሰች፤ በወቅቱም ከእቅዶች መካከል የማደናገሪያ ወይም የማምታቻ "ውል" ማዘጋጀት አንዱ ነበር።

የውጫሌ ውል በሚያዝያ 1881 ዓ.ም በአሁኑ አምባሰል ወረዳ ውጫሌ በምትባል ቦታ በዳግማዊ አፄ ምኒልክና በጣሊያኑ ንጉስ አምቤርቶ መካከል ተፈረመ። የውጫሌ ውል 20 አንቀጾች ያሉት ሲሆን አንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው ፅሁፍ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት በማጣቱ ለጦርነቱ መቀስቀስ ምክንያት መሆኑን ደግሞ የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ።

በዚህም የአንቀፁ የጣሊያንኛ ትርጉም የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካኝነት ማድረግ ይገባል የሚል ሲሆን ነገሩ ግን የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በቀጥታ በጣሊያን በኩል እንዲከናወን የሚያስገድድ ነበር።

በአንቀጽ 17 አማካኝነት ጣሊያን የውሉን ሀሳብ በጣሊያንኛ በመቀየር የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በማጥፋት የጣሊያን ሞግዚት እንድትሆን ቀዳዳ ያበጀ ነው ብለው ነገስታቱ እና መኳንንቱ ስለተገነዘቡ የውጫሌ ውልን እንደማይቀበሉት አሳወቁ።

እትጌዋም "እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ" ብለው ቆርጠው ተነሱ። ከዚህም በኋላ ንጉሰ ነገስት ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ለመላው ኢትዮጵያውያን ጥሪ አቀረቡ፤ ከአራቱም አቅጣጫ የተመመው የኢትዮጵያ ስራዊት ወረኢሉ ከትሞ እንዲጠብቅ ከንጉሱ በኩል ትዕዛዝ ተላለፈ።

የአገራቸውን መሪ ጥሪ በደስታ የተቀበሉት የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ያላቸውን ነገር ሁሉ ጥለው እምቢ ለአገሬ ብለው ንጉሱን ተከትለው ጦር አንግበው ግስጋሴያቸውን ወደ ዓድዋ ተራሮች አደረጉ።

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ንጋት ላይ አገሬን ነፃነቴን ክብሬን አላስነካም በሚል ወገን በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእብሪት ከተወጠረ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ከታጠቀ ከተቀናጀ ሰራዊት ጋር የዓድዋ ጦርነት ተደረገ።

በጦርነቱ ውጤት ጣሊያን በዓድዋ ላይ ተሸመድምዳ መውደቋ መሸነፏ በመላው አውሮፓ ሲሰማ የዜና ምንጮችም ቀዳሚ ዘገባቸው ሲያደርጉት ትልቅ አግራሞት ቢፈጥርም በተቃራኒው ደግሞ ለመላው አፍሪካውያን የመነቃቂያ በዓለም ላይ አዲስ ክስተት የማያ ጊዜ ሆነ ። ጥቁሮች በጦር ሜዳ ተሰልፈው በራሳቸው ወግና ባህል ወኔና ጀግንነት ነጮችን ማሸነፍ እንደሚችሉም የብስራት ደውል ተደወለ።

አይቻልምን ወደ ይቻላል የቀየሩ ለዓለም አዲስ ክስተትን ያስተዋወቁ ነፍሳቸውን የገበሩ አጥንታቸውን የከሰከሱ አባቶቻችን እና እናቶቻችን ውለታቸው ምን ይሆን ብድራቸውስ እንዴት ይከፈል ይሆን። ይህ ደግሞ የእኛ የአሁኖቹ ትውልዶች የምንጠይቀው ጥያቄ ነው።

የዓድዋ ድል የአፍሪካ ጦር የአውሮፓውያንን ጦር የደመሰሰበት ብቻ ሳይሆን የጥቁር ኃይሎች ከነጭ አውሮፓውያን ኃይሎች ጋር በመፋለም ታሪካዊ የበላይነትን ያስመዘገቡበት አንፀባራቂ፣ አስደናቂ አስደማሚ ብሎም ለኋላው ታሪክ ለፊተኛው ደግሞ ትልቅ ትምህርት ቤት የሆነ ድል ነው።

ዓድዋ ለሰለጠነችው ጣሊያን ታላቅ ውርደትና ሞት፣ ለነጭ አውሮፓውያን በሙሉ ደግሞ ሃፍረትና ስብራት ሲሆን ለኢትዮጵያን እና ለመላው ጥቁር ህዝቦች ደግሞ ደማቅ የድል ድል ሆኖ ዛሬም ድረስ ቀጥሏል።

የኢትዮጵያ የዓድዋ ድል ዓለምን የታሪክ አካሄድ የለወጠ ነጮች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የበላይነት ያፈረሰ ለነጭ ገዢዎች መራር የማይዋጥ ሽንፈት የሆነበት ለጥቁር ህዝቦች ግን ታላቅ ትንሳኤና የማንነት ትግል የተረጋገጠበት ነበር።

ዓድዋ የማይሰረዝ የማይጠፋ የማይቀየር እስከ ዘለዓለም ሲዘከር የሚኖር አልፋና ኦሜጋ ድላችን ነው። ዓድዋ የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ የፅናት ተምሳሌት ነው። ይህ ጽናትና አልበገር ባይነት ደግሞ በእኛዎቹ በዛሬዎቹ ትውልድ ይደገም ዘንድ በየዓመቱ የኋሊት እየተጓዝን እንዘክረዋለን።ነገር ግን ከመዘከር ባለፈ ዓድዋን ሆነን ለመገኘት ምን ያህል ጽናት አለን?

አባቶቻችን በደምና አጥንታቸው ጠብቀው ያቆዩትን ምድር እኛ በአስተሳሰባችን ካጠበብነው የቱ ጋር ነው የእነሱ ልጅነታችን ? አንድ ለመሆን የተዋደቁ እናትና አባቶቻችን አጥንትና ደማቸው አደራ ይሁነን። ለአገሩ ክብር ሲል ደረቱን ለባሩድ የሰጠው ወገኔ መንፈሱ አይውቀሰን ያንን ጊዜ እናስታውስና ለአንዲት ኢትዮጵያ ዘብ እንቁምላት።

እኛ የማን ልጆች እንደሆንን እናሰላስል የአባቶቻችንን የሞራል ልዕልና በእኛም ላይ ይታይ ። ራሳችንን እናክብር አገራችንንም በተግባር እንጥቀም። ዛሬም የዓድዋን ድል መሰል የጀግንነት ስራ ከሁላችንም ይጠበቃል።

ከጥበት ወጥተን ለአገራችን ልንሰራባቸው የሚገቡ በርካታ የቤት ስራዎች ያሉን ህዝቦች ነን። አገራችን እንደ ዓድዋው ዘመን በቀጥታ ቅኝ ሊገዟት ባይመጡም በእጅ አዙር ሊያንበረክኳት የእነሱ ተላላኪ የሆነ መንግስት ሾመው እንደፈለጉ ሊፈልጧት ሊቆርጧት የሚቋምጡ በርካታ የዓለም አገራት መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ይህንን የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ስናከሽፈው ቆይተናል አሁንም እያከሸፍነው ነው። ይህንን ለማስቀጠልም ወደፊትም ብዙ ይጠበቅብናል። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ኃይላችን የኋላውን ታሪካችንን ስንቅ አድርገን ለዛሬው ማንነታችን በአንድነት ቆመን መስራት ስንችል ብቻ ነው።

በመሆኑም እንደ ዓድዋው ጊዜ ልዩነቶቻችንን ወደጎን በማድረግና በዓለም ላይ ያለን ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአንድ አፍ ተናጋሪ በአንድ ልብ መካሪ ሆነን በመቆም ችግሮቻችን ላይ በመዝመት ዓድዋን መድገም ይጠበቅብናል።

አስቸጋሪ ነገሮችን አሸንፈን ከችግሮቻችን በላይ ሆነን በመገኘት የአባት የእናቶቻችንን አደራ የምናስቀጥል ትውልዶች ልንሆን ይገባል። ከዓድዋ ጀምሮ የኢትዮጵያን እድገት የማይመኙ ይልቁንም በተፈጥሮ ሃብቷና በልጆቿ በመነገድ መበልጸግ የሚፈልጉ ኃይሎች ዛሬም ድረስ አሉና የኋላውን ታሪካችንን እየነገርን ዛሬም የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን ደግሞ በስራዎቻችን ልናስመሰክር ይገባል። አበቃሁ!

# ሰብዓዊ ዕርዳታ በሽረ ከተማ

**ጌትነት ምህረቴ**



ሽረ፡- ከሽረ ከተማ ወደ ሽራሮ መገንጠያ መንገድ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በሚገኘው የሰብዓዊ ድጋፍ መስጫ ጣቢያ ላይ ሠዎች ተሰባስበዋል። በቡድን በቡድን ሆነውም ተሰልፈዋል። በሰብዓዊ ዕርዳታ የማከፋፈያ ጣቢያውም ስንዴ፣ ክክና ዘይት በየቦታው ተድርድሮ ይታያል። ሰብዓዊ ድጋፍ ለመውሰድ ለመጡ ነዋሪዎችም በአስተባባሪዎች አማካኝነት ስማቸው እየተጠራ ስንዴ፤ ክክና ዘይት ሲሰጥ ተመልክተናል።

የሰብዓዊ ዕርዳታ ለመውሰድ ማከፋፈያ ጣቢያና መጋዘን ቅጥር ጊቢ ውስጥ ካገኘናቸው የሽረ ከተማ ነዋሪዎች መካከል አንዷ ወይዘሮ ሙሉ ወልደገብርኤል በሽረ ከተማ 04 ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። የሰብዓዊ ድጋፉ ይቆራረጣል እንጂ በጣም ጥሩ ነው። ይህም ድጋፍ የተገኘው ሰላም በመፈጠሩ ነው ይላሉ።

"እኛ እዚህ ዕርዳታ ለመውሰድ እዚህ ተሰልፈን የምታየን ጦርነቱ ባስከተለው ችግር ተረጂ ሆነን ነው እንጂ ራሳችን ሰርተን ቤተሰብ እያስተዳደርን የምንኖር ሰዎች ነን" የሚሉት ወይዘሮ ሙሉ፤ አሁንም የተፈጠረው ሰላም ዘላቂና አስተማማኝ ከሆነ ለአጭር ጊዜ ዕርዳታው ያስፈልገን እንደሆነ እንጂ ተረጂ መሆን አንፈልግም ብለዋል።

የሰላምን ዋጋ በቃላት ለመግለጽ ያዳግታል። አሁን ሰላም በመፈጠሩ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች ዳግም ተመልሰዋል፤ የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴም እየደመቀ መሄዱ አይቀርም፤ የሰብዓዊ ድጋፉም ያለምንም ችግር አሁን እየተሰጠን ነው ሲሉም ወይዘሮ ሙሉ ገልጸዋል።

ሰላም በመናጋቱ ምክንያት ለከፋ ችግር ተጋልጠን ቆይተናል ያሉት ወይዘሮ ሙሉ፤ እኛ ሰላም ፈላጊዎች ሰርተን የምንኖር ነን። ይህ ችግር ተመልሶ እንዳይመጣ ሁላችንም የሰላም ዘብ ሆነን ልንጠብቀው ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አቶ መኩሪያ አሰፋ የሽረ ከተማ ነዋሪ ናቸው። ዕርዳታ ለመውሰድ እንደመጡ ይናገራሉ። ብዙ ችግር አሳልፈናል፤ አሁን ያለፈው አልፏል አሁን ላይ ያለው ሰላም ጥሩ ነው መቀጠል ይኖርበታል ነው ያሉት።

አሁንም በብሄር የሚከፋፍሉን፣ ለውጭ አፍራሽ ኃይሎች የሚላላኩ አይጠፉም። እነዚህን ጸረ ሰላም ኃይሎች መከላከልና ማጋለጥ ያስፈልጋል ያሉት አቶ መኩሪያ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተዋልዶ ተዛምዷል፤ በአንዳንድ ጠብ ጠንሳሾች ቅራኔ ቢፈጠር እንኳን በቀላሉ የሚለያይ ሕዝብ አይደለም። ቂም ይዞም አይቆይም፤ መንግሥትና ሕዝቡ ተቀናጅተው ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ ዕርዳታ አግኝቻለሁ የምትለው ወይዘሮ ረህመት ሙዘይን፤ ዛሬ የተሰጠን ድጋፍ እስካሁን ከተሰጡን በብዛትም በአይነትም የተሻለ ስለሆነ መቀጠል ይኖርበታል ነው ያለችው።

አሁን የተሰጠን ድጋፍ ዘይት፣ ክክ፣ ስንዴ ነው። ስለዚህ ጥሩ ጅምር በመሆኑን ይቀጥል እንላለን ብላለች። የሰላም አለመኖር ተረጂ አድርጎናል የምትለው ወይዘሮ ረህመት፤ ሰላም ሰፍኖ መንገዱ ተከፍቶ፣ አገልግሎቶች እየተሟሉና ቀጣይነታቸው እየተረጋገጠ ሲሄድ እኛም በነጻነት ሰርተን መኖር እንችላለን። ለዚህም ሰላምን ማረጋገጥ የሁሉም ድርሻ መሆኑን ገልጻለች።

በሶስተኛ ዙር ድጋፍ በመጠንም በአይነትም ከፍ ያለ በመሆኑ ሕዝቡ እፎይታ አግኝቷል። በእርግጥ ድጋፍ የሚፈልገው የከተማው ነዋሪ 274ሺህ ሕዝብ ነው። የተፈቀደልን ደግሞ 149ሺህ ሕዝብ ስለሆነም በጣም ለተቸገሩ ወገኖች ድጋፍ ማድረግ እየቻልን ስለሆነ ጅምሩ ጥሩ ነው የሚለው በትግራይ ክልል የሽረ እንደስላሴ ከተማ የአደጋና ስጋት ጊዜያዊ አስተባባሪ አቶ ሰይድ ከማል። አሁን የተሰጠው ሦስተኛ ዙር ድጋፍ ነው ብሏል።

ቀጣይም ከዓለም ምግብ ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የተሻለ ድጋፍ እንደሚጠበቅ ያለውን ተስፋም ገልጿል።

በሰላም ስምምነቱ የትግራይ ሕዝብ ተደስቷል፤ ሰላም ባይናጋ ኖሮ አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ተረጂ አይሆንም ነበር የሚለው አቶ ሰይድ። አሁን ሰላም በመፈጠሩ የተጋነነው የዋጋ ንረት እየቀነሰ መጥቷል፤ የተጠፋፋ ቤተሰብ መገናኘት ጀምሯል፣ የንግድ እንቅስቃሴው እያንሰራራ ነው፤ ድጋፉም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል የሚል እምነት አለኝ። እናም ይህ ሰላም ዘላቂ እንዲሆን ማኅበረሰቡ፣ ወጣቱ፣ ምሁሩ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች ሁላችንም የተገኘውን ሰላም ማረጋገጥ አለብን ነው ያለው።

# በሶማሌ ክልል ለድርቅ ተጎጂዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ናቸው ያሉት አቶ ደበበ፤ ለደረሰው የድርቅ አደጋ ጉዳት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ድጋፍ እያቀረበ ይገኛል።

በሶማሌ ክልል በተከሰተው የድርቅ አደጋ አራት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ተጎጂዎች በኮሚሽኑ በኩል ተለይተዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሶስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ አስቸኳይ ሰብአዊ ድጋፍ ይፈልጋል ብለዋል።

በሁሉም አካባቢዎች ለሚደርሱ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በጥናት ላይ ተመስርቶ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኅብረት እና በዓለም ምግብ ፕሮግራም በኩል ድጋፍ እየቀረበ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ ደበበ እንዳስታወቁት፤ በቦረና ዞን የተከሰተውን የድርቅ አደጋና ለመቆጣጠርና ሰብዓዊ ድጋፍ ለማቅረብ መንግሥት በትኩረት እየሰራ ይገኛል። በተለይ በቦረና ተጋላጭ ለሆኑ አጥቢ እናቶች፣ ነፍሰጡሮች፣ ህፃናትና አቅመ ደካሞች መንግሥት 18 ሺህ ኩንታል የአልሚ ምግብ ድጋፍ አቅርቧል።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁሉም አቅጣጫ በድርቅ ለተጎዳው የቦረና ዞን ሕዝብ የተለያዩ ድጋፎችን እየቀረበ ይገኛል ያሉት አቶ ደበበ፤ ሀብትን አቀናጅቶ ለመምራት፣ በአንድ ቦታ የሚፈጠር የድጋፍ ድግግሞሽ ለማስቀረትና በሁሉም አካባቢ ለሚገኙ ተጎጂዎች ድጋፉን በአግባቡ ለማድረስ የሚያስችል ጠንካራ ስራ መስራት አለበት ብለዋል።

አቶ ደበበ እንደተናገሩት፤ ለቦረና ዞን የሚቀርበውን ድጋፍ አቀናጅቶ ለመምራት ያቤሎ ከተማ ላይ የተቋቋመው የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል የመረጃ ስራና ሰብዓዊ ድጋፍ በትክክል ለማድረስ እየሰራ በመሆኑ የሚቀርቡ ድጋፎችን በማዕከሉ በኩል እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል።

በድርቅ በተጎዱ አካባቢዎች የእንስሳትን መኖ እጥረትን ለመከላከል ክልሎች እንስሳቶችን በራሳቸው ግንኙነት መሰረት ሳርና የተለያዩ መኖዎች በብዛት ወዳሉባቸው አካባቢዎች በማሰማራት ችግሩን ለመከላከል እየሰሩ ነው ብለዋል።

ከዚህ ባሻገር በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በሚገኙ ትግራይ፣ አማራና አፋር ክልሎች በአጠቃላይ 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሕዝብ በ29 አጋር አካላት አማካኝነት ድጋፍ እየተደረገለት ይገኛል። አጋር አካላት በማይሸፍኗቸው አካባቢዎች ላይ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ድጋፍ እየቀረበ መሆኑን አመላክተዋል።

በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ክልሎች በራሳቸው አቅም ድጋፍ በማቅረብ እየተወጡ መሆኑን የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተሩ፤ በራስ አቅም ችግሮችን የመቋቋም ጥረቱ የሚበረታታ መሆኑን ተናግረዋል።

# ምርትን በመያዝ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዋጋን በማናር ሕዝብን ለማነሳሳት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም ብለዋል። ምርትን ይዞ በማቆየት እና የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የፖለቲካ ቀውስ መጠቀሚያ በሚያደርጉ አካላት ላይ መንግሥት ጠንካራ ቁጥጥር እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

ምክትል ከንቲባው፤ ምርት ወደ ግብይት መውጣት አለበት። መጠነኛ የሆነ ትርፍ እስካለ ድረስ ዘላቂ የሆነውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ማሰብ ያስፈልጋል። ምርትን ይዞ በማቆየትና የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የፖለቲካ ቀውስ መጠቀሚያ ማድረግ ተገቢ አይደለም። በእንዲህ አይነት ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ ኃይሎች ከድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው። ሕግን ተላልፈው በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ መንግሥት በንግድ ሕጉ መሠረት አስፈላጊውን ርምጃ ይወስዳል።

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ አሁን ላይ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት፤ በአዲስ አበባ ከተማ ያለው ኅብረተሰብ ሰፊ የጤፍ ፍጆታ ይፈልጋል። ይህንን ለማሟላት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተጠናከረ መንገድ ምርት ወደ ከተማ እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችል ትስስር ፈጥረዋል። ለዚህም ከንግድ፣ ከገቢ፣ ከፖሊስ፣ ከደንብ አስከባሪዎችና ከማህበራት የተውጣጣ ግብረ-ኃይል የተደረጃ ሲሆን፤ ግብረ-ኃይሉ በዋናነት አቅርቦትን ማሳለጥና ሕገወጥነትን የመቆጣጠር ተልዕኮዎችን ይዞ እየሰራ ይገኛል።

በአንዳንድ አካባቢዎች ምርት ወደ ገበያ እንዳይወጣ የማድረግ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። በሌላ መንገድ ንግድ ላይ ያሉና ድለላ ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት እየገዙ የማከማቸትና ወደ ግብይት እንዳይገባ የማድረግ ሁኔታዎች አጋጥመዋል ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ በወፍጮ ቤቶች ብዙ ምርቶችን በመያዝና ወደ ግብይት የሚገባውን ውስን በማድረግ ዋጋ ሲወደድ ለመሸጥ የሚደረጉ ፍላጎቶችና ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውንም አንስተዋል። ኬላዎችን በመዝጋት ምርት በነጻ እንዳይንቀሳቀስ እና ግብይቱ እንዳይሳለጥ የሚደረግበት ሁኔታ መፈጠሩን በመጥቀስ፤ ይህም በመዲናዋ የምርት እጥረት እንዲኖር ማድረጉን ተናግረዋል።

"ከክልሎች ጋር ባለን ግንኙነት በዚህ ዓመት በቂ ምርት መኖሩንና ለፍጆታ የሚሆን ምርት እንዳለ መረጃው አለን" ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ነገር ግን ከተማ ውስጥ ላለው ኅብረተሰብ ምርቱን አቅርቦ ከመሸጥ ይልቅ በኮንትሮባንድ እንዲወጣ የሚደረግባቸው አካባቢዎች እንዳሉ ገልጸዋል።

ችግሩን ለመፍታት ከፌዴራል መንግሥትና ከክልሎች ጋር በመነጋገር በሕገወጥ መንገድ የተዘጉ ኬላዎች እየተከፈቱና ምርት የሚገባበት ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን በመጠቆም፤ ምርት በብዛት ወደ መዲናዋ ሲገባ የናረው የጤፍ ዋጋ ቅናሽ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

አስተዳደሩ የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ፤ የተማሪዎች ምገባና የሴፍቲኔት ፕሮግራምን ጨምሮ በርካታ ሥራዎችን እየሰራ እንዳለ በመጥቀስ ሕዝቡ ችግር ላይ እንዳይወድቅ የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ይዞ እየሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

# ባጃጅ ተሽከርካሪዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ገልፀው፤ ከባጃጅ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የከተማ አስተዳደሩ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ባጃጆችን በሚመለከት ምንም አይነት ታርጋ ባይሰጥም፣ ከተለያዩ ክልሎች ይዘው የመጧቸውን ታርጋዎችን እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል።

የባጃጅ የትራንስፖርት አገልግሎት መንግሥት የትራንስፖርት አገልግሎት ማድረስ በማይችልበት ቦታዎች ላይ ማለትም የከተማ ዳርቻዎች፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ አገልግሎት መስጠት እንደተጀመረ አስታውሰው፤ አሁን ላይ እየተስፋፋ መጥቶ በከተማይቱ ውስጥ ከሚገኙ 11 ክፍለ ከተሞች መካከል በስምንቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ከተማ አስተዳደሩ አገልግሎቱን ወደ አሰራር ለማስገባት ባደረገው ጥረት 9 ሺህ 950 የባጃጅ አገልግሎት ሰጪዎች በ 123 ማህበራት ተደራጅተው በስምንቱ ክፍለ ከተሞች ላይ እንደሚሰሩ ተናግረው፤ እስካሁን ብዛት ያላቸው የባጃጅ ተሽከርካሪዎች እንዳልተመዘገቡ ጠቁመዋል።

ከባጃጅ ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያይዞ በኅብረተሰቡ ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እየተከሰቱ ነው። የከተማ አስተዳደሩ ያሉትን ችግሮች በመለየት እየሰራ ነው ያሉት አቶ ምትኩ፤ ከትራፊክ ፍሰት ጋር በተያያዘ ሰፊ መስተጓጎል ይፈጥራሉ፣ ትርፍ በመጫን አደጋዎች እንዲፈጠሩ መንስኤ በመሆንና ከሕግ አስከባሪ አካላት ጋር ግጭት እየፈጠሩ ነው። ሕግን አክብሮ አገልግሎትን ከመስጠት አኳያ ሰፊ ክፍተቶች እየታየባቸው እንደሆነ አቶ ምትኩ አብራርተዋል።

በኅዳር ወር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ፣ የሰላምና ፀጥታ እንዲሁም የከተማው ፖሊስ ኮሚሽን በጋራ በመሆን የባጃጅ ማህበራትን ጠርተው እንዳወያዩና ከተማ አስተዳደሩ በሚወስንላቸው ታሪፍ ሊሰሩ እንደሚገባ፣ በዋና ዋና መንገዶችና አደባባዮች ላይ መስራት እንደማይችሉና የከተማ አስተዳደሩ በሚፈልግበት ጊዜ ከመስመር ላይ ሊያስወጣቸው እንደሚችል ከስምምነት መደረሱን አስታውሰዋል።

የከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ቢሮ ይህንን መነሻ በማድረግ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶችን ዘርግቷል። ከእዚህም መካከልም ታሪፍ የመወሰን፣ የሚመሩበትን መመሪያ የማዘጋጀት፣ የስምሪት ቦታዎችን የመለየት፣ ባለ ንብረቶችን በማኅበር የማደራጀት ስራዎች ተሰርተዋል።

"የከተማ አስተዳደሩ በፖሊሲውና በእቅዱ የባጃጅ ትራንስፖርትን የመጠቀምና የማስፋፋት ምንም አይነት ፍላጎት የለውም" ያሉት አቶ ምትኩ፤ ባጃጆች መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ በማይሆንባቸው የከተማዋ አካባቢዎች ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ስለሆነ በዛው ይቀጥሉ ተብሎ ተወስኖ እንደነበረና መስመር አንለቅም፣ በሚወጣው ታሪፍ አንሰራም የሚሉና የመደራጀት ፍላጎት አለመኖር ትልቁ ችግር እንደሆነ ተናግረዋል።

የከተማ አስተዳደሩ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን የስምሪት መስመሮች የለየ ሲሆን በከተማዋ ዳርቻዎች፣ በሰፋፊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ በተመረጡ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ መደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት በሌለባቸው ቦታዎች ላይ የስምሪት መስመሮች ሊሰጡ እንደሚችሉና ተመዝግበው ከተደራጁት ውጭ መስመር የመስጠትም ሆነ የማደራጀት ተግባር ከዚህ በኋላ እንደማይኖር አቶ ምትኩ ጠቁመዋል።

የከተማ አስተዳደሩ በሚያወጣው የታሪፍ ተመን፣ በሚሰጠው ስምሪት፣ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ብቻ መስራት እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

# ነፃ ሃሳብ

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## “የሽግግር ፍትሕ “ሲባል... !?

ባለፈው ሳምንት ሰኞ በሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ላይ የሚመክር አገር አቀፍ ጉባኤ የመክፈቻ ስነ ስርዓት በመዲናችን በአዲስ አበባ ተካሂዷል። ይሄን መጣጥፍ እያጠናቀርሁ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ሁለተኛው ምክክር የተካሄደ ሲሆን ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ዳግሞ ባለፈው አርብ ተካሂዷል። በቀጣይም በመላ አገሪቱ በ56 መድረኮች ላይ ለሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ረቂቅ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። በዛሬ መጣጥፌ ስለ ሽግግር ፍትሕ ምንነት፣ አስፈላጊነትና አላባውያን አነሳሳለሁ። እግረ መንገዴንም ከጽንሰ ሀሳቡ ጋር እተዋወቃለሁ።

የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲው ጆን ኤልስተር ፤”Transitional Justice in Historical Perspective”በሚል ርዕስ ባስነበበን ማለፊያ መጽሐፉ ፤ የሽግግር ፍትሕ ትላንት የተጀመረ ሳይሆን የ”ዴሞክራሲ” ጽንሰ ሀሳብ መቀንቀን ከጀመረበት ከዛ ጥንታዊ ዘመን አንስቶ የነበረ ነው ሲል ይሞግታል ። በ411 ዓመተ ፍዳ/ዓመተ ዓለም/ እንዲሁ ከ404 እስከ 403 ዓዓ በአቴንስ በወቅቱ የነበረው “ዴሞክራሲያዊ”አካሄድ በአምባገነኖች ተገልብጦ እያለ ስራ ውለው የነበሩ ፈላጭ ቆራጭ አሰራሮች ፤ አምባገነኖች ከአገዛዝ እንዲወገዱ ሲደረግ ተሽረው የነበሩ ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች ተመልሰው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

በራሽያ የጥቅምት፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ድህረ አብዮቶችም ተመሳሳይ ክስተቶች መኖራቸውን በማስረጃ ያወሳል። በቅርብ ደግሞ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከጀርመን ናዚ፣ ከጣሊያን ፋሺዝምና ከጃፓን ሽንፈት በኋላ በዘመኑ አውድ የሚበየን የሽግግር ፍትሕ መተግበሩን ጆን ኤልስተር ያስታውሳል። በቀጣይ ዓመታት ደግሞ አገራችንን ጨምሮ በላቲን አሜሪካ ፣ በደቡብ አፍሪካ ፣ ዚምባቡየ ፣ ሩዋንዳ ፣ ቡልጋሪያ ፣ ሮማኒያ ፣ ሀንጋሪ ፣ ግሪክ ፣ ጣሊያን ፣ ስፔን ፣ ወዘተረፈ እንደየ አገራቱ ነባራዊ ሁኔታ የሽግግር ፍትሕ ተተግብሯል ይለናል ጸሐፊው ።

ናኦሚ ሮት አሪያዛና ሀቪየር ማሬዝኩሬና በጋራ ባሳተሙት ፤”Transitional Justice in the Twenty-First Century Beyond Truth”በተሰኘው መጽሐፋቸው ደግሞ የሽግግር ፍትሕ ወጥ የሆነና ቁርጥ ያለ ብያኔ ባይኖረውም ፤”ጨቋኝ ፣ ፈላጭ ቆራጭና አፋኝ ከሆነ አገዛዝ መወገድ ማግስት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፣ ግፎችና ሰቆቃዎች ከሁለንተናዊ ፍትሕ አንጻር የሚታዩበት አግባብ ነው ።”ይሉናል ። የሽግግር ፍትሕ ማለት በቀደመው ጨቋኝ ወይም አፋኝ አገዛዝ ወይም በአንድ ረዘም ላለ ጊዜ በተካሄደ የእርስ በርስ ጦርነት ወይም ግጭት ወቅት መሠረታዊ የሰው ልጆችን መብት የጣሱ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ፤ ከጦርነቱ በኋላ በዳይና ተበዳይ፣ የተለያዩ የማኅበረሰቡ አካላትን በሚወክሉ ግለ ሰቦች በተዋቀረው የማሕበረሰብ “ዳኞች” ፊት ቀርበው ይቅር የሚባባሉበት ሂደት ነው ።

የሽግግር ፍትሕ አላማ በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት አገናኝቶ ፤ በዳዩ በድርጊቱ መጸጸቱን በሕዝብ ፊት ይቅርታ ሲጠይቅና ፣ ተበዳዩም ፣ የበዳዩን ከልብ የመነጨ ጸጸት ተረድቶ ከልብ ይቅርታ እንዲያደርግ ሲሆን የረጅም ጊዜ ዓላማው ግን ፤ የፖሊቲካም ሆነ ማኅበረሰባዊ ሥልጣንን ተጠቅሞ ሰብዓዊ ፍጡርን መበደል ወንጀል መሆኑ ታውቆ ቀጣዩ ትውልድ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈጽምና በዳይና ተበዳይም ከልብ ይቅር ተባብለው ለወደፊት ቂምና በቀል ለአገሪቷ ሰላምና ለማኅበረሰቡ ዕድገት ጠንቅ እንዳይሆኑ ለማድረግ ነው ።

የሽግግር ፍትሕ ከመደበኛው የፍትሕ ሂደት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ እንጂ የሚተካ አይደለም ። የሽግግር ፍትሕ ተፈጻሚነቱ በተለምዶ በዝቅተኛ ደረጃ በደል በፈጸሙት ግለ ሰቦች ላይ እንጂ በዋነኞቹ (ባለ ሥልጣናት) መብት ጣሾች ላይ አይደለም። እነሱ በመደበኛው ወይም በልዩ ችሎት ይዳኛሉ። በሌላ አነጋገር የበዳይና ተበዳይ ፊት ለፊት ተገናኝቶ በማኅበረሰቡ ፊት ይቅርታ መጠየቅና መቀበል በምንም መልኩ አንድን በዳይ በተለይም “የወንጀል

> አገርን ለመጠበቅ፣ ለመታደግና ለማዝለቅ በማሰብ የሚደረጉ የይቅርታና የእርቅ ሂደቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማስታወስም ይህ ግን ሊሆን የሚችለው የተለወጠ ስርዓት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው :: ግጭቶችና ጦርነቶች ሙሉ በሙሉ ባልተቋጩበት ሁኔታ የሽግግር ጊዜ ፍትህን ለማስፈን ይቻላል ወይ ሲሉ ብዙዎች ያጠይቃሉ

ድርጊቶቹን ያቀነባበሩትንና የመሩትን” ከመደበኛው ፍርድ ቤት ፍትሐዊ ብይን ነፃ አያደርጋቸውም ።

የሽግግር ፍትሕ በተለምዶ ማኅበረሰብ ከሚያስተናግዳቸው የፍትሕ ሂደቶች ለየት ያለና በጥቂት አገራት ብቻ በተግባር የተተረጎመ ሲሆን ስኬታማነቱና ውጤታማነቱ ላይ ውስንነት አለበት ። ካሉበት ውስንነቶች አንዱ ተበዳይን በተፈለገው ደረጃ መካስ አለ መቻሉ ነው ። ይህ የፍትህ ሂደት በአፍሪካ ውስጥ በሰፊው በተግባር የተተረጎመው በደቡብ አፍሪካና በሩዋንዳ ሲሆን በመንግሥት ደረጃ እንደ ስኬት ቢቆጠርም በተበዳይ ግለ ሰቦችና ዘመዶች ዘንድ ግን ካሳ ባለመካተቱ ቅሬታ መተው አልቀረም ።

ሰዎች በተፈጥሮ ተጨባጭ የሆነ ካሳ ፈላጊ ስለሆኑ በዳይና ተበዳይን ፊት ለፊት አገናኝቶ ይቅርታ አጠያይቆና አስተቃቅፎ ማለያየቱ ብቻ የተበዳዩን ውስጣዊ ቁስል ሊጠገግ አልቻለም ። የደቡብ አፍሪካም ሆነ የሩዋንዳ የፍትሕ ሥርዓት ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት የጸዱ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ፤ ለዚህ አይነቱ ውስንነት ተጠያቂ ራሱ የሂደቱ መሪ ነው ብሎ ያምናል።

የሽግግር ጊዜ ፍትሕ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የሚተገበር የፍትህ ሂደት ነው። የፍትሕ ሚኒስቴር ሰነድ ደግሞ ፤ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት መዘርጋት ዘላቂ ሰላም ፣ እርቅ እና ፍትሕ በማስገኘት ረገድ ውጤታማ መሆኑንና በግጭት ፣ በጦርነት ወይም በሌላ ምክንያት ለተፈፀሙ ጥቃቶች ፣ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና በደሎች የተሟላ መፍትሔ ይሰጣል ሲል ይተነትናል። ለሀገሪቱ የታሰበው የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የሚመራበትንና ሥራ ላይ የሚውልበትን የማስፈፀሚያ ስልቶቹ ፣ ክስ ፣ እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማድረግ ፣ ይቅርታና እርቅ ፣ ምህረት እና ካሳን ያካተተ ነው ።

የሽግግር ፍትሕ ሥርዓት መዘርጋት ዘላቂ ሰላም ፣ እርቅ እና ፍትሕ በማስገኘት ረገድ ውጤታማ መሆኑንና በግጭት፣ በጦርነት ወይም በሌላ ምክንያት ለተፈፀሙ ጥቃቶች ፣ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና በደሎች የተሟላ መፍትሔ እንደሚያመላክት የፖሊሲ ሰነድ ያትታል። በሌሎች አገራት ክስ እና ቅጣት ዋነኛ የሽግግር ፍትሕ ማስተግበሪያ ስልቶች ሆነው መታየታቸውንም ሰነዱ ያብራራልና ፖሊሲው ግን ከክስ እና ቅጣት ባለፈ እውነት እየተጣራ ይፋ የሚሆንበት፣ ዘላቂ እርቅ የሚሰፍንበት ፣ የማካካሻ እርምጃ እና የተቋማት ለውጥ የሚካሄድበት ነው ።

የፖሊሲው አጥኚ ቡድን አባል አቶ ምስጋናው ሙሉጌታ ፤ የሽግግር ፍትሕ በሚከተሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አስፈላጊ መሆኑን ያወሳሉ ። ኢትዮጵያ የምትገኝበት አገራዊ አውድ ማለትም የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፣ አለመረጋጋት፣ ግጭትና የእርስ በርስ ጦርነት በመቀጠሉ ዜጎች ለሞት፣ ለመፈናቀል አደጋ እየተጋለጡ በመሆኑና ለነዚህ ችግሮች ከዚህ በፊት የተሰጡ ምላሾች ሙሉ አለመሆናቸው የአጥፊዎችና የተጎጅዎችን ቁጥር ማብዛቱ ፣ የበደሎች መደራረብ እና የጥፋቶች ማህበረሰባዊ ቅርጽ መያዝ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት እና አካሄድ ፍትሕ መስጠትንም ሆነ ይቅርታ እና እርቅን ማከናወን አላስችል ማለቱ የመጀመርያው ነው ።

የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ለሀገረ - መንግሥት ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ ማለትም ባለፉ በደሎች ይቅር ለመባባልና እርቅ ለማውረድ ብሎም እየተከፋፈለ ያለውን ሕዝብ ለማቀራረብ ግንኙነትን ለመጠገን ፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና እርቅን ለማውረድ ለዚህም የሰውን ክብር ለመመለስ፣ ላለፈ ቁስል እውቅና ለመስጠት እንዲሁም ለዳግም ውህደት ማነሳሳት ሁለተኛው አላማ ሲሆን የተሳካ የሽግግር ፍትሕ ሂደት ሳይተገበር የዴሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማስፈን የማይቻል መሆኑ እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር እና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያግዝ መሆኑ ሶስተኛው ሲሆን አራተኛው አላማ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ያለው የማይተካ ሚና ነው ። ነገር ግን በሽግግር ፍትሕ ውስጥ የገለልተኛ ወገን ተሳትፎ መሠረታዊ ጥያቄ ነው ።

ይህንን የሽግግር ጊዜ ፍትሕ ማስፈፀሚያ ሆነው ከቀረቡ ስልቶች ደግሞ ዋነኛው ክስ ነው። ማን ይከሰሳል የሚለውም ዋነኛ ነጥብ ነው። እውነትን ማፈላለግ እና ይፋ ማድረግ፣ እርቅ ፣ ምህረት፣ ማካካሻ ወይም ለደረሱ የመብት ጥሰቶች ብሎም የሀብት ውድመቶች ውጤታማና ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም ሌላ ካሳ ፣ መጠገኛ ፣ ማደሻ ማገገሚ አፈጻጸምን በተመለከተ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ያካትታል።

የሽግግር ጊዜ ፍትህ “ጥቂት ጥፋተኞችን በወንጀል አስቀጥቶ ከሚገኘው ያለፈ ፍትህ” ይገኛል ተብሎ የሚታሰብበት ስርዓት ነው የሚሉት የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹና የህግ ባለሙያው አቶ አምሃ መኮንን ደግሞ ቀድሞ ከነበረ አንድ ስርዓት ወደሚታሰብ ሌላ አዲስ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚደረግ ሽግግር ነው ሲሉ ይናገራሉ።

በዚህ ሽግግር ውስጥ የሚታዩ የከፋ የመብት ጥሰቶች እንዴት ይዳኙ የሚለው ምላሽ በሽግግር ፍትህ እንደሆነም ይገልጻሉ። አቶ አምሃ የሽግግር ጊዜ ፍትሕ በመደበኛው የፍትህ ስርዓት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙና በመቶዎች ወይም በሺዎች የሚቆጠሩ ጥፋተኞች ሲኖሩ እንደየጥፋት ደረጃቸው ተጠያቂ ለማድረግ ይቅር የሚባለውን ይቅር ለማለት የሚተገበር መሆኑንም ያነሳሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህሩ ደመላሽ ሽፈራው (ፒ ኤች ዲ) ፤ ከሕወሓት ጋር የተደረገው ደም አፋሳሽ ጦርነት ጨምሮ በተለያዩ ጊዜያት ከበድ ያሉ የተለያዩ ጥሰቶች ሲፈጸሙ ነበር። በጥሰቶቹ ለህልፈተ ህይወት ከተዳረጉት ባሻገር ለተለያዩ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች የተዳረጉ እልፍ አእላፍ ናቸው ። ልክ እንደተጎጂዎቹ ሁሉ የጥሰቶቹ ዓይነትና ፈጻሚዎቹም ብዙ ናቸው። እነዚህን በሙሉ የወንጀል ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም ። በመሆኑም የሚፈለገውን ፍትህ ጨምሮ ቂምና ቁርሾዎችን በእርቅና በተለያዩ መንገዶች ለማስቀረት ከመደበኛው የዳኝነት ስርዓት የተሻገረ የሽግግር ጊዜ ፍትህን ማስፈን ያስፈልጋል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን መቋቋሙንም የህግ መምህሩ ያስታውሳሉ፤ ምንም እንኳን ኮሚሽኑ የተጠበቀውን ያህል ሚና ለመጫወት ባይችልም። የሽግግር ጊዜ ፍትህ “በለውጥ ማዕቀፍ ውስጥ ነው ሊታሰብ የሚችለው” የሚሉ ወገኖችም አሉ። ሁሉም በእኩልነት ሊጠየቅ የሚችልበት እና ወደ ቀጣይ አዲስ ምዕራፍ የሚገባበት ነው። ሆኖም መሰረታዊ ለውጥን ታሳቢ አድርጎ ያለፈውን ስርዓት ችግሮች በተወሰነ መልኩ ምላሽ የሚሰጥበት እንጂ ዝም ብሎ ሂሳብ የማወራረድ ነገር አይደለም ሲሉ ያስገነዝባሉ ።

አገርን ለመጠበቅ፣ ለመታደግና ለማዝለቅ በማሰብ የሚደረጉ የይቅርታና የእርቅ ሂደቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ በማስታወስም ይህ ግን ሊሆን የሚችለው የተለወጠ ስርዓት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው ። ግጭቶችና ጦርነቶች ሙሉ በሙሉ ባልተቋጩበት ሁኔታ የሽግግር ጊዜ ፍትህን ለማስፈን ይቻላል ወይ ሲሉ ብዙዎች ያጠይቃሉ። በሽግግር ፍትህ ስም የተበዳዮች የፍትህ ጥያቄ ተድበስብሶ ሊቀርና ወንጀለኞችም ተገቢውን ቅጣት ሳያገኙ ሊቀሩ ይችላሉ ብለው የሚሰጉም እንዲሁ። የሽግግር ፍትህ የግጭት መፍቻ አካል ነው ።

ይህ ግን በግልጽ ተለይቶ የተቀመጠ ዓላማን ይፈልጋል። ከዚህ አንጻር የተፈጸሙ በደሎችን መርምሮ አጣርቶ እውነቱን ማሳወቅ በራሱ አንዱ የፍትህ አካል ሊሆን ይችላል እንደ ምሁሩ ገለጻ። ሆኖም ይህ ሲሆን የወንጀል ተጠያቂነት ሰፍኖ ነው። ከሽግግር ፍትሑ ጎን ለጎን በተለይ በህገ መንግስቱ ይቅርታና ምህረትን የማያሰጡ ከባድ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ማድረግ የግድ ነው።

ይህን በማረጋገጥ የተበዳዮችን ጥያቄ ከመመለስም በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ በሂደት እርቅ ሊያመጡ የሚችሉ የገንዘብና የሌሎች የዐይነት ካሳዎች ሊደረጉም ይችላሉ። ፍትህ ውስጥ የከፋ ጉዳት የደረሰበትን የማህበረሰብ ክፍል በተለያዩ የማህበራዊ የማከሚያ መንገዶች በልማት ተጠቃሚ በማድረግ መካስ እንደሚቻልም ይጠቁማሉ። የሽግግር ፍትሕ ሕዝብ ሰፊና አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙበትን መነሻ ምክንያት ወይም መግፍኤ ወደ ኋላ ተመልሶ አበጥሮ የሚለይበትና ወደፊት እንዳይደገሙ በጋራ መፍትሔ የሚያመላክትበትና ለተፈጻሚነቱም ቃል ኪዳን የሚገባበት አግባብ ነው ።

የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠቂዎችንና ሰለባዎችን አማክሎ የሕግና የፖለቲካ ክፍተቶች የሚመለከት ሒደት ነው ። ይህ ታላቅ ተግባር በመላ አገሪቱ ወጥ በሆነ አግባብ እንዲተገበር ደግሞ የማስፈጸሚያ ፖሊሲ ያስፈልጋል ። አሁን ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር የሚካሄደው ምክክር ለሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ረቂቅ ዝግጅት ግብዓት የሚያሰባስብ ነው። የፖሊሲ ግብዓት የማሰባሰቡ ሒደት ከረቂቅ ግብዓትነት መጀመሩ ከዚህ ቀደም ከተዘጋጁት ፖሊሲዎች ለየት ያደርገዋል። ረቂቁ ሲዘጋጅም ሆነ ለማጽደቅ መሰል ውይይትና ምክክር ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# የጨረቃ ንባብ ያፈራቸው የትምህርት በሬዲዮ መሐንዲስ

**ሰላማዊት ውቤ**

ለገዳዲ ሬዲዮ ጣቢያ ሲነሳ ታሪካቸው ከጣቢያው ጋር በብርቱ የተቆራኘ ነውና በለጠ ከተማም አብረው ይወሳሉ:: ዛሬም በዕድሜ ጫና ለዛውን ባላደበዘዘው ጀሮ ገብ ድምጻቸው በተማሪዎችና በአርሶ አደሩ ዘንድ አብዝተው ይታወሳሉ:: አርአያ በሆኗቸው የጥበብ ሰዎችና በእግራቸው በተተኩ ጋዜጠኞችም እንዲሁ ይነሳሉ:: በተለይ ከሦስት አሥርተ-ዓመታት በላይ የማስተማር ቆይታቸው በተማሪና በአርብቶና አርሶ አደሩ ሕይወት ውስጥ ተጨባጭ ለውጥ አምጥተዋልና ልዩ ቦታም ይሰጣቸዋል:: እኛም ለዛሬ የዛሬ ስምንት ዓመት በጡረታ እስከ ተገለሉ ድረስ በዚህ መልኩ ለተማሪው፤ ለአርሶና አርብቶ አደሩ እንዲሁም የጥበብ ሰዎችንና ጋዜጠኞችን በማፍራት ሲያገለግሉ የቆዩትን የመምህርና የለገዳዲ ትምህርት በሬዲዮ ጋዜጠኛ በለጠ ከተማ ማሙዬ አርአያነት ያለው ተሞክሮ ለማካፈል እንግዳ አድርገናቸዋል::

**ውልደትና ዕድገት**

እንግዳችን መምህርና ጋዜጠኛ በለጠ ከተማ ውልደትና ዕድገታቸው በቀድሞው ሸዋ ጠቅላይግዛት ቅንብቢት ወረዳ ነው:: የተወለዱት በ1949 ዓ.ም ሲሆን ወላጆቻቸው የሚያርሱና የሚያሳርሱ አርሶ አደሮች ነበሩ:: እናታቸው ከቤተ- ክህነት የቀሰሙት ትምህርት ዘመናዊ ትምህርትን እንዲናፍቁ ስላደረጋቸው ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ያስገቧቸው ገና በህፃንነታቸው ነበር:: ሲያስገቧቸው ሁሌ ባይዋቸው ቁጥር ልጆቼ እንደነዚህ ቢሆኑልኝ እያሉ በውስጣቸው መንፈሳዊ ቅናት የሚያሳድሩባቸውን መምህራን እንዲሆኑም ይመኙ ነበር:: ምንም ህፃናት ቢሆኑም በተለይ እሳቸውን ‹‹ተምረህ መምህር ነው ምትሆንልኝ››ይሏቸው ነበር::

የአካባቢው ልጅ ትምህርት ቤት የሚገባው ከጎረመሰ በኋላ ስለነበር በመሆኑም ወላጅ አባታቸውም ሆኑ የአካባቢው ሰዎች ‹‹እንዴት እነዚህን ላይና ታች አቅጣጫን እንኳን ለይተው የማያውቁ ህፃናት ትምህርት ቤት ትልኪያለሽ››እያሉ ገስፀዋቸው ነበር:: እነዚህ ልጆች ትልልቅ በመሆናቸውና ከእርሻ ሥራ ላይ ተነስተው ትምህርት ቤት በመግባታቸው ሞፈር ሰቀል የሚባሉበት ሁኔታ ነበር::

ባለቤታቸውም ሆኑ ጎረቤት ያንን ይበሉ ይሄን እናታቸው በትምህርትም ሆነ በሌላ ጉዳይ አቋማቸው የማያወላውል ቆራጥ ነበረና እሳቸውም ሆኑ ወንድማቸው በህፃንነት የገቡበትን ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ ቀጠሉ:: ትምህርት ቤቱ ከመኖርያ ቀያቸው ራቅ ያለ ነበርና እየተመላለሱ የእናታቸውን ምኞት እውን ለማድረግ መማሩን ተያያዙት:: እንደ ዛሬው መማርያ መጻፍም አልነበረም:: እንዳሁኑ ኢንተርኔትና ቤተ-መጽሐፍት መኖርማ ፈፅሞ አይታሰብም!:: የእነሱ ቤተ-መጽሐፍት እርሻው፤ ሳር ቅጠሉና ሜዳው እንደነበርም ያስታውሳሉ:: እንዲህም ሆኖ የተማሩትን ትምህርት የማስታወስ ከፍተኛ ችሎታ ነበራቸው::

ምንም ሳያስቀሩ የተማሩትና ያዩትን በሙሉ ልቅም አድርገው ነበር የሚይዙት:: ትምህርታቸውን ሸኖ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አሀዱ ያሉት እንግዳችን የእናታቸውን ምኞት ገና በልጅነታቸው ግብ ለማድረስ ቆርጠው የተነሱ ይመስል:: ከክፍሉ ሁሉ አንደኛ በመውጣት በሁለት ዓመት ውስጥ ስድስተኛ ክፍል መግባት ቻሉ:: ደብል እንዲመቱ ይደረግ የነበረውም ፈተና እንኳን ሳይፈተኑ መምህሮቻቸውና የትምህርት አመራሩ በችሎታቸው ተማምኖባቸው መሆኑ ከዕድሜ አቻዎቻቸው ተማሪዎች አልፎ የትምህርቱን ማህበረሰብ በእጅጉ የሚያስደምም ሆነ::

በተለይ ከሦስተኛ ክፍል ወደ ስድስተኛ ክፍል በአንድ ጊዜ የተዘዋወሩበትን ሁኔታ ዛሬም እንደማይረሱት ያወሳሉ:: ከታች ክፍል ጀምሮ ያስተማራቸውና ጉብዝናቸውን የሚያውቀው አንድ መምህር የአምስተኛ ተማሪዎችን ሲያስተምሩ አንድ ጥያቄ ይጠይቋቸዋል:: ሆኖም ጥያቄውን ሁሉም አልመለሱም:: ‹‹ቆዩኝ ይህን ጥያቄ የሚመልስ የሦስተኛ ክፍል ተማሪ አመጣላችኋለሁ›› አሉና በለጠን ወደ አምስተኛ ክፍል አስጠሯቸው:: የመምህሩ ጥያቄ ከአፋቸው እንደወጣ ትንታጉ ተማሪ ጥያቄውን በትክክል መለሱ:: ይሄን የሚከታተለው ርዕሰ መምህር በአጠቃላይም መምህራኑና የትምህርት አመራሩ ለምን ስድስተኛ ክፍል አስገብተን አናየውም ተባባሉ:: በአንድ ጊዜም ደብል መጥተው ስድስተኛ ክፍል ገቡ::

ስድስተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ፈተና የሚወሰድበት መሆኑ



ፎቶ፡- በለጥሻቸው ልዑልሰገድ

መምህርና ጋዜጠኛ በለጠ ከተማ

በነሱ ጊዜ ገና የተጀመረ አለመሆኑ ቀናቸውና በዚሁ ዓመት መጨረሻ በጥሩ ውጤት ወደ ሰባተኛ ክፍል አለፉ:: ‹‹ይሄን ዓይነቱን ብቃትና ችሎታ ለመገንባት ያበቃኝ በጨረቃ አጠና የነበረ መሆኑ ነው›› ይላሉ እንግዳችን በትምህርት የመጎበዛቸውን ምስጢር ሲገልፁት:: በወቅቱ ታዲያ በአካባቢያቸው አንዳንድ ሻል ያለ ኑሮ ያላቸው ነዋሪዎች ዘንድ ኩራዝን ጨምሮ ክትክታ የሚባል እንጨት ነው እንደ ጧፍ ለብርሃን አገልግሎት የሚውለው:: እነ በለጠ ቤትም ኩራዝ ቢኖርም ከቤተሰባዊ አገልግሎት ባሻገር ለትምህርት ወዳዱ ታዳጊ ጥናት የሚውል አልነበረም:: በመሆኑም ያላቸው አማራጭ በጨረቃ ማንበብና ማጥናት ነበር::

ወላጆቻቸው አመሻሹ ላይ ከብት ለማብላት ከቤት ሲወጡ ደብተራቸውን በመያዝ አብረዋቸው ወደ መስኩ ይሄዳሉ:: ወላጅ እናታቸው ታዲያ ተግባራቸውን በማበረታታት የሚቀድማቸው የለም:: ብዙ ጊዜም ለዚሁ ተግባር ያነሳሷቸዋል:: ቀን ሲፅፉ የዋሉትን ሁሉ ማታ ደግሞ በጨረቃ ብርሃን ያነቡታል፤ እንደ ውዳሴ ማርያም በመደጋገምም ይሸመድዱታል:: እኩለ ሌሊቱን አልፈው እስከ ንጋቱ በንባብ የሚዘልቁበት አጋጣሚ በርካታ ነበር:: እንግዳችን ብቻ ሳይሆኑ ታላቅ ወንድማቸውም አብሯቸው በጨረቃ ያነቡ ስለነበር ምን ይመጣብኛል ብለው ስጋት እንዳልነበራቸው ያስታውሳሉ::

‹‹ ወላጆቼ የሚያርሱ ብቻ ሳይሆኑ የሚያሳርሱም ስለነበሩ ከሌሎች በተለየ ትንሽ ሀብት ነበራቸው›› የሚሉት ጋዜጠኛ በለጠ፤ ይህም ቢሆን እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ብዙ ፈተናዎችን ለማለፍ ግድ ብሏቸው እንደነበር አይሸሽጉም:: ‹‹ጫማ ስላልነበረን ትምህርት ቤት የምንሄደው በባዶ እግራችን ነበር፤ ያም ቢሆን እግራችን ጠንካራ ስለነበር አብዝተን የጨርቅ ኳስ እንረግጥ ነበር›› ሲሉም ያስታውሳሉ::

እንግዳችን እንደሚሉት፤ ያኔ ኃይለማርያም ማሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስመ ገናና እና ደረጃው ከፍተኛ በመሆኑ መግባት ቀርቶ በአጠገቡ ማለፍ ለብዙ ለአካባቢያቸው ነዋሪዎች ብርቅ ነበር:: ጥበቃው እንኳን እዛ በመሥራቱ የሚኮራበት ሁኔታ ይስተዋላል:: ታዲያ በጨረቃ ማጥናታቸውና ጎበዝ ተማሪ ለመሆን መብቃታቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ቤት እንዲከታተሉ አስችሏቸዋል:: ያስተማሯቸው ህንዶችና ሌሎች የውጭ ዜጎች በበኩላቸው ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት እንዲኖራቸው አድርገው ቀርፀዋቸዋል:: የቋንቋ ክህሎታቸው በጨረቃ ሳይቀር ትጉህ አንባቢ መሆናቸው በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ዩኒቨርሲቲ መግባት የሚያስችል ነጥብ እንዲያመጡ አግዟቸዋል::

ሆኖም በወቅቱ ወላጅ አባታቸው ድንገት በሞት ስለተለይዋቸውና ቤተሰብ የማስተዳደሩ ኃላፊነት በእርሳቸው ላይ ስለወደቀባቸው ዩኒቨርሲቲ ገብተው መማር ባለመቻላቸው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ:: በተለይ የአባታቸው እርሻ እንደሳቸው ትኩስ ኃይል ያለው የጎበዝ ጉልበት የሚያስፈልገው ነበር:: የኋላ የኋላ ታዲያ በምክክር እርሻ ሥራውን ታላቅ ወንድማቸው ከእናታቸው ጋር እየተጋገዙ ሊሰሩት ተስማምተው እንግዳችን እናታቸው ሲመኙላቸው በነበረው የመምህርነት ሙያ ለመሰማራት ውሳኔ ላይ ደረሱ:: አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ወደ የሚገኘው ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም በመግባትም የአንድ ዓመት የመምህራን ኮርስ በመውሰድ ስልጠናውን አጠናቀቁ::

**የሥራ ዓለም**

አብዛኛውን ዕድሜያቸውን የገፉት በማስተማር ሥራ ነው:: መምህርነት ሙያን በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሬዲዮም አሳምረው ሰርተውበት ነው ለጡረታ የበቁት:: በተለይም የቋንቋ ብቃታቸው ከፍተኛ በመሆኑ በክፍልም ሆነ በሬዲዮ ያስተምሩበት የነበረው ቋንቋ በአብዛኛው እንግሊዝኛ የነበረ መሆኑን ያነሳሉ:: በመምህርነት በቆዩባቸው ዓመታትም በጠንካራና ትጉህ ሰራተኝነታቸው በስራ ባልደረቦቻቸውም ሆነ በተማሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እንደነበራው ይነሳል::

**በፈተና የታጀበው የሥራ ስምሪት**

መምህርና ጋዜጠኛ በለጠ የአንድ ዓመቱን የመምህርነት ሙያ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በቀጥታ በሙያው ተሰማርተው እንዲሰሩ ወሎ ክፍለሃገር ተመደቡ:: የወሎ ጉዞ እጅግ አሰልችና አድካሚም እንደነበረ የሚያነሱት እንግዳችን ሲያወሩት ቀርቶ ሲያስቡት ዛሬ የሆነ ያህል ልባቸው በድካም ፍስስ እንደሚልባቸው ይገልፃሉ:: በተለይ ከደሴ ቦረና መካነ ሰላም የምትባል ከተማ የተጓዙበት ትልቅ ፈተና ያለበት እንደነበር ይናገራሉ:: በተለይም ለተከታታይ አራት ቀናት ያውም ደግሞ ሌትና ቀን መጓዛቸው እጅግ አሰልችና አድካሚ እንደነበር ነው ያመለከቱት::

በእግራቸው ከተጓዙት ከ60 መምህራን መካከል በዕድሜ ትንሹ እሳቸው ስለነበሩ በጉዞው በከፍተኛ ሁኔታ ተዳክመው ነበር:: ስልጠናውን ወስደው ሊመደቡ የቻሉትም በዕድሜያቸው ላይ አምስት ዓመት ጨምረው እንደነበር ይናገራሉ:: በእግር ለመጓዝ የተገደዱበት ምክንያት ወደ ከተማዋ መኪና ባለመግባቱ ነው:: በእርግጥ ይሄን ታሳቢ አድርጎ አውሮፕላን ተመድቦላቸው ነበር:: ሆኖም አውሮፕላኗ የምታርፍበት የአካባቢው አርሶ አደሮች ዙሪያውን መንጥረው እንደነገሩ የደለደሉት ነው:: ዝናብ ሲዘንብ ይጨቀያል:: እነሱ የተጓዙበት ወቅት ገና የክረምቱ ዝናብ በወጉ ያልደረቀበት በመሆኑ አውሮፕላኗ ዝቅ ብላ እርጥብ መሆኑን አይታ ሳታርፍ በመሄዷ ነበር::

በመሰረቱ አውሮፕላኗ ብታርፍም እንኳን ከ30 ሰው በላይ የሚጭን አቅም አልነበራትም:: ይህን ታሳቢ አድርጎ ለአንድ ሰው ሁለት በቅሎ ተመድቦላቸው 40 በቅሎ አከራዮችን ጨምሮ 100 ሆነው ነበር ጉዞውን የተያያዙት:: በአንዱ በቅሎ ታጣፊ አልጋቸውን ጨምሮ አንሶላ ብርድ ልብስ፤ ፍራሽና ሌሎች ጓዞቻቸው ተጭነዋል:: በአንዱ ደግሞ አልፎ አልፎም ቢሆን እነሱ እየወጡ የሚጓዙበት ነበር:: በአብዛኛው መንገዳቸው ላይ ወባ፤ ራቅ ሲሉም ደግሞ ኃይለኛ ሽፍታ እንዳለ በመንገደኛ እየተነገራቸው ነበር የሚያልፉት::

እንግዳችን በዚህ አስቸጋሪ ውጣ ውረድ አልፈው ቦረና መካነ ሰላም ከተማ ደረሱ:: እናም የመምህርነት ሥራቸውን እንግሊዝኛ ትምህርት በማስተማር አሀዱ አሉ:: እዚህች ከተማ ኑሮ በጣም ርካሽ ነበር:: በአንድ ብር አራት ዶሮ ከእነ እንቁላሉ በአንድ ብር እንዲሁም ዓይን እያየ ከኑግ ተጨምቆ የሚዘጋጅ አንድ ሊትር ዘይት በአንድ ብር ይገዛል:: በግም 20 ብር ባልሞላ ገንዘብ አርዶ መብላት ይቻላል:: ሁሉም እዛው በቅርብ አሉ:: የሌለው ስኳር፤ ጨውና ክብሪት ብቻ ነበር:: ታዲያ አራት ሆነው አንድ ምድርና ፎቅ ያለው ጓሳ የጎዘጎዘበት የጭቃ ቤት ተከራዩ:: ለዚህ ሁሉ አራቱ ጓደኞሞች ታዲያ ከነቀለባቸው ያዋጡ የነበረው እያንዳንዳቸው 25ብር ብቻ ነበር:: ለቤት ሠራተኛ የሚከፍሉት ደግሞ አምስት ብር ነው:: የአካባቢው ሰዎች እንዴት ይህን ያህል ገንዘብ ትከፍሏቸዋላችሁ ብለው ተቃውመዋቸው ነበር:: ነገር ግን እዛ አካባቢ መምህር ሚስት ከሌለው የትኛውም አባወራ ከሚስቱ ስለሚጠረጥረውና ችግር ሊያደርስበት ስለሚችል የቤት ሠራተኛ መቅጠር ግድ ነበር::

አብዛኞቹ የሚቀጠሩት ደግሞ ‹‹እንደ ገረድ (ቤት ሰራተኛ) በደሞዝ፤ እንደ ሚስት በ80›› በሚል የውል ስምምነት ነበር:: ቦረና ላይ ያሉት ሴቶች በአብዛኛው በጣም ቆንጆዎች ስለነበሩ በሠራተኛ ተቀጥረው በቀናት ውስጥ መምህራኑ ሚስት ያደርጓቸውና ወልደው ከብደው የሚቀሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው:: እሳቸው ይህን ቀድመው ሰምተው ነበርና በለጠ ይህችንስ አይለቃትም እየተባሉ ቢኖሩም ልጅነቱ፤ ከቤተሰብ መለየቱ፤ ትራንስፖርት አለመኖሩና የቤተሰብ ናፍቆት ምሬት ሁሉም በአንድነት ዝውውር ጠየቁና በቆነጃጅቶቹ የቤት ሠራተኞች ተጠልፈው እዛው ሳይቀሩ ከመካነ ሰላም ከተማ ወደ ደሴ ከተማ ተዛወሩ:: ከደሴም ቃሉ አውራጃ ገርቢ በቶ ምትባል ስፍራ ተመድበው ለአንድ ዓመት ያህልም በኃላፊነት ሰሩ:: ከዚህ በኋላ ደግሞ ዝውውር ጠየቁና ለደሴና ለኮምቦልቻ ከተማ ቅርብ ወደነበረችው አርቡ መጡ:: በዚህች በተመቻቸች ከተማም አምስት ዓመት ሰሩ::

በደርግ ዘመን መምህርነት በተመደቡበት ፊደል ማስቆጠር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሥራዎች መሳተፍም ጭምር ነበር:: መምህር ከማስተማር በመለስ በትምህርት ቤቱ ያሉትን ክበቦች ማጠናከር ይጠበቅበታል:: በቀበሌም መሳተፉ ግዴታ ነበርና በቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ደግሞ ሰብሳቢ ነበሩ:: ልጅ ቢሆኑም ውሳኔያቸው ጥሩ ነበርና በደስታ ነው ያሳለፉት:: መሰረተ ትምህርት ይወጡና አርሶ አደሩን ያደራጁም ነበር:: እንግዳችን በዚህ መልኩ በመምህርነት ካገለገሉ በኋላ ሥራቸውን በመልቀቅ ፊታቸውን ወደ ትምህርት ደግሞ አዞሩ:: መምህራን ኮሌጅ በመግባትም ትምህርታቸውን መከታተሉን ተያያዙት:: ሁለት ዓመት ተምረውም ተመረቁ::

ዳግም ወደ መምህርነት ሙያ ተመለሱና ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በመመደብ በአንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ቤት ለአንድ ዓመት አስተማሩ:: እዚህም ዝውውር ጠየቁና ከደቡብ ወደ ሰሜን ሸዋ በመሄድ ቀድሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩበት ኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ለሁለት ዓመታት ሲያስተምሩ ቆዩ:: እዚህ እያስተማሩ አርሶአደሩ በሬዲዮ መማር ያለበት መሆኑን የሚያሳስብ ማስታወቂያ ሰሙ:: ይህ ማስታወቂያ ከክፍል መምህርነት ወደ ሬዲዮ መምህርነት ያሸጋገራቸው ነበር::

### የለገዳዲ ሬዲዮ ፕሮግራም

እንግዳችን እንደሚናገሩት፤ በዚህ ጣቢያ የመምህርነት ሙያቸው ደብዛው ሳይጠፋ ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ለ28 ዓመታት በሬዲዮ በማስተማር አገልግለዋል:: እሳቸው ይሰሩ የነበረው በዋናነት የጎልማሶች ግብርና፣ አጠቃላይ ትምህርትና በኋላ የትምህርት አምባ የተባለው ቅዳሜን ከእኛ ጋርና እሁድን ለአንድ አፍታ ፕሮግራም ላይ ነበር:: አርሶ አደሩ በሬዲዮ መማር እንዳለበት የሚገልፀውን ማስታወቂያ ሰምተው ዝም አላሉም:: ‹‹ለእኔ ነው የወጣው›› በማለት ፈጥነው ተመዘገቡ:: ተመዝጋቢው ከፍተኛ ቢሆንም እሳቸው ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አልፈው ትምህርት በሬዲዮ ላይ ተመደቡ:: ከቅጥሩ በፊትም ከእንግሊዝ አገር በመጡ ባለሙያ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል:: ከዚህ ስልጠና በኋላ የሸዋ ክፍለ አገር ትምህርት ቤት ጽሕፈት ቤት ውስጥ ተቀጥረው የ‹‹ትምህርት በሬዲዮ››ሥራ ጀመሩ:: ሥራው በግብርና፤ ጤና እና ፖለቲካ ላይ ያተኮረ ነበር::

‹‹እኔ እያልኩ ብናገርም ሥራው በጋራ የሚሰራ ነው›› የሚሉት እንግዳችን ትምህርት በሬዲዮ የሚሰጠውም ለጎልማሳ አርሶ አደሮች እንደነበርም ያወሳሉ:: እንዳከሉትም እሳቸው የሚያዘጋጁት የሬዲዮ ፕሮግራም ግብርና ላይ ያተኮረ ነበር:: ግን ደግሞ እርሻውን ብቻ ሳይሆን የአርሶ አደሩን ጤና፤ የአኗኗር ዘይቤና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴውን ይዳስሳል:: እሳቸውም ሆኑ ሌሎች ባልደረቦቻቸው በሚያዘጋጅዋቸው የለገዳዲ ትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም የከተማውን ከገጠር የገጠሩን ከከተማ መቀላቀል ፈፅሞ አይታሰብም:: ፕሮግራሙ በሰፊው አርሶ አደርና የገጠር ሕብረተሰብ በራሱ ቋንቋና በራሱ አካባቢ እሴትና ማህበራዊ መስተጋብር እየተዘጋጀም ነበር የሚቀርብለት::

ምሳሌዎች ሁሉ ከአካባቢው የወጡ አልነበሩም:: ኦሮምኛ ለሚናገር በኦሮምኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶና ተተርጉሞ፤ አማርኛ ለሚናገረው ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶና ተተርጉሞ ይቀርብለታል:: ይሄን እሴትና የማህበራዊ መስተጋብር ለማየት ፕሮግራሙን ከማዘጋጀታቸው በፊት በየአካባቢው ዞረው ያጠኑ ነበር:: ዕቅድ የሚያቅዱትም በዚሁ መልኩ እንደነበር ያወሳሉ:: ይሄን መሰረት አድርጎ መቅረብ፤ አለመቅረቡም አየር ላይ ከመዋሉ በፊት በብርቱ የሚገመገምበትና ግብረ መልስ ያካተተ የአሰራር ስርዓትም የነበረው ነው:: የተቀረፀውን ፕሮግራም ግብርና ሚኒስቴር ወስደው ለባለሙያዎቹ የሚያሰሙበት ሁኔታም ነበር:: በዚህም ፕግራሙ ከቋንቋም ሆነ ከይዘት አንፃር የአካባቢውን አርሶ አደሮች በቀጥታ ተደራሽ የሚያደርግ መሆኑን አስቀድመው የሚያረጋግጡበት ሁኔታ መፍጠር ችለዋል:: አየር ላይ የሚያውሉትም ባለሙያዎቹ ‹‹ልክናችሁ ይስማማናል›› ካሏቸው በኋላ መሆኑንም አውግተውናል::

መዝናኛ ሙዚቃ የማስጨፈር ፕሮግራም ሳይሆን በተለያየ አካባቢ ሕብረተሰቡንና አርሶ አደሩን እንዲሁም ተማሪዎችን የሚይዙና በሬዲዮ የሚሰጠውን ትምህርት እያዋዙ በማጀብ የሚያጣፍጡላቸውን ወቅታዊና ዘመናዊ ነበሩ:: መደበኛ ትምህርት፤ ትምህርት ቤትን፤ ተማሪዎችን መምህርን፤ የትምህርት ቤቱን ጥበቃና ጊቢውን በሙሉ የሚዳስስ ፕሮግራም መሆኑንም ያነሳሉ:: ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀውን ስርዓተ-ትምህርት መሰረት አድርጎ ተማሪዎች በክፍል ብቻ ሳይሆን በሬዲዮ እንዲማሩ ተደረገ:: በዚህ ወቅት ታዲያ እሳቸው ሁለተኛ አራተኛ እና ስድስተኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ያስተምሩ ነበር::

ይህን ፕሮግራም ተማሪው ብቻ ሳይሆን መምህሩም ይማርበት የነበረ እንደሆነ ያነሳሉ:: ታዲያ በየአካባቢው በመዞር ‹‹በሬዲዮ ፕሮግራም እንዲካተት የምትፈልጉትን ፕሮግራም ንገሩን›› በማለት ይጠይቃሉ:: ይሄን ብታስተናግዱ የሚሉትን አስተያየትም ይሰበስባሉ:: በዚህ ፕሮግራም ተሳታፊ ልጆች ይጋበዛሉ:: መምህራን በአብዛኛው ከበድ የሚሉ ርዕሶችን የተለያዩ ድምጾችን ይጠቀማሉ:: እዚህ ላይ ተማሪዎችን በስፋት በማሳተፍ ይሰራ እንደነበርም ይጠቅሳሉ:: ጽሑፍ ከየአቅጣጫው የሚመጣ ሲሆን ለሚደርሱት ደብዳቤዎችም ምላሽ ይሰጣል::

### አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት

እንግዳችን ይሄን ያዘጋጁ የነበሩት ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በላይ የሆኑና ትምህርት ቤት ሄደው ለመማር አቅም ለሚያንሳቸው ተማሪዎች ሲሆን ጫማ የሚጠርጉ፤ ተቀጥረው በቤት ውስጥ ህፃናት የሚያሳድጉና ማታ ማታ ወላጆቻቸው ትምህርት ቤት ሲልኳቸው ለትምህርት ቤት በካሴት ተቀርፆ ይላክላቸው እንደነበር ያስታውሳሉ:: ‹‹ምክንያቱም የአየር ሰዓት ስለሚጣበብ አይገኝም:: ታዲያ ፕሮግራሙ እነዚህን ዕድሜያቸው የገፋ ልጆች ሁለተኛ ክፍል ያስገባል:: ጊዜ ሳይወስዱ በሁለት ዓመት ውስጥም አራተኛ ክፍል ይደርሳሉ›› ሲሉም ያብራራሉ::

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ የፕሮግራሙ አዘጋጅም ባልደረቦቹ በተሰበሰቡበት ፕሮግራሙን አቅርቦ የሚገመገምበት አለ:: ቴክኒሻኑ በራሱ ካለው ልምድ አንፃር ገምግሞ እንደገና እንዲዘጋጅና እንዲቀረጽ ያደረግም ነበር:: በተለይ የግብርና ፕሮግራማቸው የግብርና ሚኒስቴር ሠራተኞች የማይደርሱበትን ሁሉ ተደራሽ ያደርጋል:: ስምንት ኪሎ ግራም የሚመዝነውን የሬዲዮ መቅረፀ ድምፅ ተሸክሞ መጓዝ ብርቱ ድካም ቢያስከትልም የጋዜጠኝነትና የማስተማር ፍቅሩ ነበራቸውና ድካሙን ይታገሱና ይችሉት ነበር:: ከሚያስተላልፏቸው ፕሮግራሞች መካከልም የጎልማሶች ግብርና፤ ቅዳሜን ከእኛ ጋር፤ እሁድን ለአንድ አፍታ፤ መደበኛ ትምህርት የፕሮግራሙ መጠሪያዎች ነበሩ:: ቃለ መጠይቅ፤ ጭውውት፤ መነባንብ፤ ድራማን ጨምሮ በጽሑፍ የሚቀርብ ንባብ፤ ደብዳቤዎችና መጣጥፍ ለፕሮግራሙ ተደራሲያን መልዕክት የሚተላለፍባቸው ዘዴዎች ናቸው::

በተለይ በመደበኛ ትምህርት በሚያቀርቡት ፕሮግራም ሴትና ወንድ ተማሪዎችን የሚተቹበት እንደነበር አንስተው፤ ሴት ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንሄዳለን ብለው ከቤት ከወጡ በኋላ ዩኒፎርማቸውን መንገድ ላይ ቀይረው ከትምህርት ቤት በመቅረት የሚሄዱበትን ሁሉ በዝርዝር ይነሳበት እንደነበር ይገልፃሉ:: በእነዚህ ፕሮግራሞች ዙርያ ጽሑፍ፤ መጣጥፍ፤ ጭውውት፤ ግጥም ድራማና ትዝብት የሚያቀርቡ የውጭ ጸሐፍትንም በፕሮግራማቸው ያሳትፉ ነበር:: ዙበይዳ አወል፤ ቤተልሔም ክፍሌ፤ ዮሴፍ ምርኩዝ፤ አርቲስት ሠራዊት ፍቅሬ፤ ኮሜዲያን ደረጀ ኃይሌ ከሚያሳትፏቸው ውስጥ ይጠቀሱ እንደነበርም ያስታውሳሉ:: ያኔ ለነዚህ ተሳታፊዎች ይከፈል የነበረው አምስት ብር መሆኑንና ይሄም የእሳቸው የጣት ፊርማ የነካው ክፍያ በወቅቱ ከፍተኛ የተሳታፊ ክፍያ እንደነበርም ይገልፃሉ::

### የጎልማሶች ግብርና ፕሮግራም

በዚህ ፕሮግራም ስለ እርሻ፣ ስለ ከብት፣ እንስሳትና ዶሮ እርባታ፣ ስለ ንብ ማነብ በተለያየ መንገድ ለአርሶ አደሩ በዲዮ ትምህርት ይሰጣል:: አርሶ አደሩ በዚህ ግንዛቤ እንዲጨብጥ ለማድረግም የሚከተሏቸው የተለያዩ ስልቶች ነበሩ:: አንዱና ዋንኛው አርሶ አደሩ ሬዲዮ አግኝቶ ትምህርቱን የሚያዳምጥበትን መንገድ ማመቻቸት ሲሆን ይሄም የእነርሱ ድርሻ ነበር:: እናም ከግብርና ጽሕፈት ቤት ጋር በጋራ በመሆን አርሶ አደሩ ሬዲዮ የሚያደምጥበትን ጣቢያ ያዘጋጃሉ::

'አኒሜትር ጋይድ' ብለው የሚጠሩት አንዱ ነው:: ይህም እራሱን የቻለም ፕሮግራም ሲሆን ከአካባቢው አርሶ አደሮች በዕውቀቱ ሻል ያለ አርሶ አደር የሚሳተፍበትና ሕብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲጨብጥ የሚያደርግበት ነው:: በዚህ አሰራር በየአንዳንዱ ገበሬ ማህበር አንዳንድ ሬዲዮ ይሰጣል:: ሬዲዮኖቹ ከውጭ በብዛት ስለገቡ እጥረት ባለመኖሩ ኮታው በሁሉም ገበሬ ማህበራት ተደራሽ ነበር:: በዚህ ገበሬ ማህበር በየአንዳንዱ ገበሬ ማህበር የሚኖረውና ከሌሎች አርሶአደር ነዋሪዎች ሻል ያለ ዕውቀት ያለው ሰው ታዲያ ሬዲዮኑን ቤቱ የማሳደርም ዕድል ይሰጠዋል:: እናም የአካባቢው አርሶ አደሮች ወደ እሱ እየመጡ ለተወሰነ ሰዓት እንዲያዳምጡ ስብሰባ እንዲያደርጉና በሥራቸው ዙርያ እንዲወያዩ ይጠራል:: ከፕሮግራም ስርጭቱ በፊት በስርዓት ያስቀምጣቸዋል:: በስርጭት ወቅት ማውራት የለም አድምጡ ይላቸዋል:: ከስርጭት በኋላ ‹‹ዛሬ ምን ምን ያዛችሁ?›› ብሎ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል:: ይህ አቀራረብ በትምህርት ቤቶችም በተመሳሳይ የሚሰራበት የነበረ ሲሆን፤ ተማሪዎች ምን ያህል እውቀት እንደጨበጡ የሚመዘንበትም ነበር:: ታዲያ ቀስ በቀስ አርሶ አደሩ ባመቸውና ይህን ታሳቢ አድርጎ ተደለደለለት ሰዓት ወደ ጣቢያው እየመጣ የሬዲዮ ፕሮግራሙን ያዳምጣል:: ሰውየው ሬዲዮኑን ዘግቶ ምን እንዳዳመጡም ይጠይቅና በዚህ መልክ አርሶ አደሩ ሬዲዮኑን ማዕከል አድርጎ ስለ ምርታማነት፤ ስለ እንስሳት ማዳቀል፤ ምርታማ ለመሆን መጠቀም ስላለበት ግብዓት እርስ በእርስ ሀሳብና ተሞክሮዎችን በመለዋወጥ ይማማራል::

### ፕሮግራሙ በአርሶ አደሩ ዘንድ ያመጣው ለውጥ

ፕሮግራሙን የጀመሩ ሰሞን ግን አርሶ አደሩ አቅሙን ባለመገንዘቡ ይሄን እንዲያደርገ ማስቻል በፍፁም ተስኗቸው ነበር:: እርሻ፤ አጨዳ፤ ጉልጓሉ አለብኝ፤ ይሄን ሥራየን ትቼ አልመጣም እያለ የሚያስቸግርበት ሁኔታ ነበር:: ቀስ በቀስ ከዚህ በመውጣቱ በብዙ መልኩ ተጠቃሚ ሆኗል:: ለምሳሌ ፕሮግራሙን በቁም ነገር የሚከታተሉበትና በተለያየ አጋጣሚ ባይኖር እንኳን ለምን አልኖረም? ብለው የሚጠይቁበት ሁኔታ ነበር:: ላሚ ስትደራ ወይም የመዳራት ፍላጎት ስታሳይ ማዳቀያ ጣቢያ መጥተው ለማዳቀል በቅተዋል:: ሁሉም ከጭቃ የተሰራ የነበረ ባህላዊ የንብ ቀፏቸውን በአንጨትና በሌሎች የቀየሩበትም አለ:: በእንስሳት እርባታ፤ በመኖ አጠቃቀም፤ በቤት አያያዝና ጽዳት እንዲሁም በአመጋገብ ስርዓት ለውጥ ያመጣበትን ሁኔታ ፈጥሯል::

የአኗኗር ዘይቤውን በማሻሻል ረገድም ለውጥ አምጥቷል:: ለምሳሌ ባህላዊ የጭቃና የሣር ቤቶቹን ወደ ቆርቆሮና ወደ ተሻለ ደረጃ ማስቀየር፤ ልጆቹን የማስተማር ልምድ እንዲያዳብር ማድረግ፤ ዘመናዊና ምርታማ የእርሻ መሣሪያዎችን እንዲጠቀም ማድረግ አስችሏል:: ብዙ አርሶ አደሮች ስልጣኔ ገብቷቸው ወደ ከተማ በመምጣት ጭምር ቤት እየሰሩ ኑሯቸውን ለማዘመን የቻሉበትን ዕድል ፈጥሯል::

እንግዳችን እንዳከሉልን ሬድዮ ሞገድ አያግደውም:: ተራራውን፤ አየሩን አቆራርጦ ሄዶ ወደ አርሶ አደሩ ጆሮ ይደርሳል:: ምቹና ቀላል ከዋጋ አኳያም እንደ ቴሌቪዥን ውድ አይደለምና አርሶ አደሩ አብዝቶ ሲያደምጠው በመቆየት ተጠቅሞበታል:: በቅቶበታል:: ፕሮግራማቸው ተወዳጅ ከመሆኑ አንፃር በየጊዜው ይደገም ይባል ሁሉም ነበር:: በሰንዳፋ መስመር ከአዲስ አበባ 30 ኪሎ ሜትር ላይ የሚገኘው የለገዳዲ የሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያ የደብዳቤ ማህደርና ስነ-ሕዝብ እንዲሁም ለአገር ውለታ የዋሉና ቀደም ያሉ ሰዎች የሚታወሱበት የነበረ መሆኑንም ያነሳሉ:: ከማስታወሻ ደብተር የሚል ፕሮግራም ነበራቸው::

### ተግዳሮት

እንግዳችን እንደሚናገሩት፤ ያኔ እንደ ዛሬው የኢንተርኔት አቅርቦት አለመኖሩ ድካማቸውን አብዝቶባቸዋል:: እንደዛሬው የሚፈልጉትን ርዕስ በኢንተርኔት ባለማግኘታቸውና ዘመኑ የተመቻቸ ባለመሆኑ አንድ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ብዙ ቦታ ይረግጣሉ:: በተለይ የጎልማሶች ግብርና የተጀመረ ሰሞን ፕሮግራሙን እንደ ተራ ወሬ ማየት ፤ ‹‹ሥራ ፈቶች፤ ሥራ ፈትቶ የእነሱን ወሬ ማን ያዳምጣል››በማለት ማጣጣልና አለመቀበል ነበር:: የማድመጥ ተነሳሽነትና ፍላጎት በፍፁም አልነበረም:: በአካባቢ ያሉ ተሰሚ አርሶ አደሮች ሬዲዮ በሚደመጥበት በየገበሬ ማህበሩ ከተመደቡ በኋላ ደግሞ ላለመምጣት እርሻ አለብኝ፤ አጨዳ አለብኝ እያሉ ማሳበብ ሁሉ ነበር::

ከፕሮግራም ዝግጅት ጋር ተያይዞ ትምህርታዊ ፕሮግራም ላይ በተለይ ቃለ-ምልልስ ማዘጋጀቱን የሚያከብድባቸው ሁኔታ ይገጥማቸው ነበር:: የቀጠራቸው ሰው በቀጠሮ ስለማይገኝላቸው ቢሮው በራፍ ላይ ቆመው የሚጠብቁበት አጋጣሚ ብዙ ነበር:: ስብሰባ ላይ ናቸው የሚባልበትና ያልሆነ ምክንያት በማቅረብ የቃለ ምልልሱ ቀጠሮ የሚሰረዝበትና የሚያቀርቡት በማጣት የሚቸገሩበት ሁኔታ ይከሰታል:: ተጠያቂዎቹ የሚጨነቁበትና ገና መቅረፀ ድምፅ ሲያዩ የሚርበተበቱበት ሲገጥማቸው ቆይቷል:: አንድ አውራጃ ሄደው የገጠማቸውንም በማሳነት ያነሳሉ:: ታዲያ እዚህ አንድ አውራጃ አውራጃ ማታ ጥያቄ ሰጥተውት ጠዋት ለቃለ-ምልልስ የቀጠራቸው የእንስሳት ሐኪም ቃለ ምልልሱን ሲጀምሩ ይርበተበትና ላብ በላብ ይሆናል:: ላቡን አንዴ በመሐረብ ሲጠርግ ሌላ ጊዜ የሚፈልገው ዕቃ የጠፋበት ይመስል ጠረጴዛውን ሲያመሳቅልና ጊዜያቸውን ሲፈጅ በጉዳዩ ላይ የተጻፈ ነገር እንዲሰጣቸው በማድረግ ቃለ-ምልልሱን ትተውት የተመለሱበት አጋጣሚ አለ::

### መቋጫ

‹‹ብዙ ተማሪዎች በሰውነት ማጎልመሻ የትምህርት መስክ አይገቡም:: ምክንያትም ስፖርት ሲባል ኳስ መርገጥ ብቻ እንጂ የአዕምሮና የሰውነት ክፍል ሥራ አይመስላቸውም›› የሚሉት እንግዳችን በጡረታ ሙያቸውን ሊሰናበቱት አቅራቢያ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ለሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅነት ማስታወቂያ ሲያወጣ ተወዳድረው መሥራት መጀመራቸውን ያወሳሉ:: በዚሁ መካከል ቢ.ፒ.አር መጣና ደግሞ ሲሰሩ የኖሩበት ጎልማሶች ስርዓተ-ትምህርት ላይ ባለሙያ ሆነው በተመደቡበትና ሲሰሩ በቆዩበት ወቅት ነው ጡረታ የወጡት:: ቀድመው ጡረታ የመውጣታቸው ምክንያት ለመጀመርያ ጊዜ መምህርነት ሲቀጠሩ የመጀመርያ ደረጃ ላይ ደብል ደብል አልፈው በመምጣታቸው ዕድሜያቸው ለቅጥር ባለመድረሱ በአንድ ጊዜ አምስት ዓመት ጨምረው በመቀጠራቸው ነበር::

አሁን ላይም ጎልማሶችን ኑሯቸውን በሚያሻሽልና በሕይወታቸው ላይ መሰረታዊ ለውጥ በሚያመጣ በተግባር ተኮር ትምህርት የማገዝና አምስቱን ዓመት ዕድሜ በሥራ የሚያካክስ ዕቅድ ነድፈው ለመተግበር ዝግጅት ላይ ይገኛሉ:: እንግዳችን ዕቅዳቸው ይሳካ መልዕክታችን ነው::


ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## ስፖርት ቱሪዝም- እየተነቃቃ ለመጣው ዘርፍ ተጨማሪ አቅም

**ዳግም ከበደ**






በዓለማችን ላይ የሚካሄዱ የቱሪዝም ነክ ስፖርታዊ ሁነቶች ከፍተኛ ምጣኔ ሃብት የሚንቀሳቀስባቸው ናቸው። “ግሎባል ማኔጅመንት ኮንሰልታንት ኤቲ ኬርኒ” የተባለ ተቋም ዘርፉ በዓለማችን ምጣኔ ሃብት ላይ የ620 ቢሊዮን ዶላር ድርሻ እንዳለው በጥናቴ አረጋግጫለሁ ይላል። ይሄ በጥቅል የቱሪዝም ዘርፍ ካለው 4ነጥብ5 ትሪሊዮን የአሜሪካ ዶላር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ ንኡስ ዘርፍ እንደሆነም አያይዞ ገልጧል።

መዋለ ነዋይን በማንሸራሸር ከሚኖረው ተፅእኖ ባሻገር የስፖርት ቱሪዝም የአገራትን የመስህብ ስፍራና መዝናኛዎች እንዲሁም ለጉብኝት ተመራጭ የሆኑ አካባቢዎችን ለማስተዋወቅ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር እንደሆነ “The Impact of Sports Tourism & Future Trends” በሚል ርእስ ስር የወጣው ፅሁፍ ያመለክታል።

### ስፖርት ቱሪዝምና ምጣኔ ሃብት

መዝናኛን፣ የጤና መሻሻልንና ውድድርን መሰረት የሚያደረጉ ስፖርታዊ ሁነቶች ማህበረሰቡ ውስጥ በቀጥታ ምጣኔ ሃብታዊ አቅም በመፍጠር ልዩ ድርሻ ያበረክታሉ። በጉዞና በጉብኝት ኢንዱስትሪ ውስጥ ስፖርትን መሰረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ጉብኚዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እድገት እያሳዩ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለዚህ ነው “የአክቲቭ ሚዲያ” ቡድን አባላት “በሰራነው ዳሰሳዊ ጥናት በየዓመቱ ቢሊዮን ዶላር እንደሚንቀሳቀስ አረጋግጠናል” በሚል ሃሳባቸውን የሚሰጡት።

ፕሉንኬት (Plunkett Research Group) የተባለ አጥኚ ቡድን ዘርፉ ላይ ባደረኩት ዳሰሳዊ ጥናት አገኘሁ ባለው መረጃ መሰረት የዓለም ዋንጫን፣ ኦሎምፒክንና የአውሮፓ ዋንጫን የመሳሰሉ ተወዳጅ ስፖርቶችን ጨምሮ ዓለማችን ላይ በሚካሄዱ ሁነቶች ምክንያት አገራት ረብጣ ገንዘብ ያወጣሉ። በምላሹ ግን በርካታ ቢሊዮኖችን ከስፖንሰር፣ ቱሪስቶችና መሰል አካላት ያገኛሉ።

“አይ ኢ ጂ” የተባለ የስፖርት አማካሪ ተቋም በበኩሉ በስፖርትና ስፖርት ቱሪዝም ላይ በዓለማችን የሚደረገው የስፖንሰር ሺፕ አሃዝ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ነው። አሁን ላይ ይህ አሃዝ ወደ አራት ነጥብ ስድስት ተመንድጎ 60 ነጥብ 1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ደርሷል።

ስፖርታዊ ሁነቶች በንግድ፣ በጤናና በመዝናኛው ዓለም ላይ ተፈላጊ እየሆኑ በመምጣታቸው ይህንን መሰረት ያደረገ የቱሪዝም ጉዞ በፍጥነት እድገት እያሳየ መጥቷል። እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2030 አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች በልዩ ልዩ ክፍሎች ስፖርታዊ ሁነቶች ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ይጓዛሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይሄም አሁን ካለው መጠን ስድስት በመቶ ጭማሪ ያሳያል።

ይህንን አሃዝ በገንዘብ ቀይረን ስናስቀምጠው የበለጠ ምስል የሚሰጠን ይሆናል።

የብሄራዊ ስፖርት ኮሚሽን ማህበራት (ኤን ኤ ኤስ ሲ) ሰራሁት ባለው የዳሰሳ ጥናት በአሜሪካን አገር ብቻ የስፖርት ቱሪዝምን መሰረት አድርገው ከተጓዙ 25 ሚሊዮን ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ስምንት ነጥብ 96 ቢሊዮን ዶላር እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ2015 ዓመት ብቻ ተገኝቷል። ይህ አሀዝ የሚያሳየው በዘርፉ ጠንከር ያለ ሁነት የማዘጋጀትና የማስተዋወቅ ሥራን ማከናወን ከተቻለ አገራት ምጣኔ ሃብታቸውን የሚደግፍ አቅምን ከስፖርት ቱሪዝም ማግኘት እንደሚችሉ ነው። ከዚህ ባሻገር ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የመስህብ ሃብቶቻቸውን ለቀሪው ዓለም በማስተዋወቅ ገፅታቸውን መገንባትም ይችላሉ።

### ኢትዮጵያ- የስፖርት ቱሪዝም

ኢትዮጵያ በስፖርቱ ዓለም ክፍለ ዘመን ያስቆጠረ ልምድ አላት። በተለይ በዓለም መድረክ ላይ ባንዲራዋን እያውለበለቡ የሚገኙ ብርቅዬ አትሌቶች የሚገኙባት ነች። አትሌት አበበ ቢቂላ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ ማሞ ወልዴ፣ አትሌት ሻለቃ ሃይሌ ገብረ ስላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ መሰረት ደፋር፣ ጥሩነሽ ዲባባና ሌሎችም ተወዳጅ አትሌቶች በዓለም አደባባይ የኢትዮጵያ ስም ገኖ እንዲሰማ ምክንያት ከመሆን ባሻገር በአትሌቲክ ስፖርት እምቅ አቅም እንዳላት ያሳዩ ናቸው። ይህ እውነት አሁንም ድረስ የዘለቀና ኢትዮጵያ የአትሌቶች መፍለቂያ መሆኗን ያስመሰከረ ነው።

በዚህ ምክንያት ምቹ የመለማመጃ መልከዓምድር ለማግኘትና የኢትዮጵያውያንን አገር ለመጎብኘት ጥቂት የማይባሉ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎች የስፖርት ቱሪዝምን መሰረት አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ።

በተጨማሪም በታዋቂው አትሌት ሻለቃ ሃይሌ ገብረስላሴ በተመሰረተውና ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረው “ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ” ላይ ከአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እንዲሁም ከመላው ዓለም የሚመጡ ጎብኚዎች፣ በኢትዮጵያ መቀመጫቸውን ያደረጉ ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮችን ጨምሮ ለጤናና ለደህንነት እንዲሁም መዝናናትን መሰረት ያደረጉ በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ተሳታፊ ይሆናሉ።

ምንም እንኳን የአትሌቲክስ ስፖርት የአንበሳውን ድርሻ ቢወስድም የስፖርት ቱሪዝምን መነሻ በማድረግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ልዩ ልዩ ስፖርቶች እየተስፋፉ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ውስጥ ተራራ መውጣት (ሃይኪንግ)፣ የብስክሌት ቱር፣ የወንዝ ላይ የጀልባ ቀዘፋ (ራፍቲንግ) ይጠቀሳሉ። በዚህ መነሻ ምክንያት የስፖርት ቱሪዝም ሁነቶች ላይ የሚሳተፉ የአገር ውስጥና የውጪ አገራት ጎብኚዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደመጣ መረዳት እንችላለን። የስፖርት ቱሪዝም በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ለማድረግ እየተሰሩ ካሉ የቅርብ ጊዜ ሙከራዎች መካከል አንዱን በምሳሌነት እናነሳለን።

### ቱሪዝም ሚኒስቴር

የቱሪዝም ሚኒስቴር የገበያ ልማትና ግብይት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት መስሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ የስፖርት ቱሪዝም አቅም ለመጠቀም የሚያስችሉ የአሰራር ማዕቀፎችን እያዘጋጀ እንደሚገኝ በያዝነው ዓመት የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በተካሄደበት ወቅት መግለጻቸው ይታወሳል። ይህ መረጃ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ በስፖርት ቱሪዝም ዘርፍ በዓለም ላይ የሚንሸራሸረውን ከፍተኛ ገንዘብ ተጫርታ ምጣኔ ሃብታዊ ጥቅሙን ለማግኘት ከምታደርገው ጥረት ባሻገር መልካም ገፅታን ለመገንባትና የቱሪስት መስህብ ስፍራዎችን ለማስተዋወቅ እንደምትሰራ ነው።

ባሳለፍነው ሳምንት በሃዋሳ ከተማ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ባካሄደው የግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ ከልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍሎች በስፍራው ከተገኙ የአገር ውስጥ የስፖርት ቱሪዝም ተሳታፊዎች ባሻገር 300 የሚደርሱ የውጪ ዜጎች ተገኝተዋል። ይህንን አቅም ለማሳደግና ማህበረሰቡ ከዚህ መሰል ሁነቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከውድድር አዘጋጁ ጋር በትብብር እየሰራ እንደሚገኝ ይፋ አድርጓል። ሃዋሳን የመሰሉ የቱሪዝም መስህብ በስፋት የሚገኝባቸው መሰል ከተሞች ላይም ተሞክሮውን ለማስፋት በጋራ ይሰራሉ።

### ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ

ዳግማዊት አማረ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ ነች። ታላቁ ሩጫ በአዲስ አበባ ከሚያካሂደው ዋናው የጎዳና ላይ ሩጫ በተጨማሪ በሃዋሳ ለ11ኛ ጊዜ ስፖርት ቱሪዝምን መሰረት በማድረግ የግማሽ ማራቶን የአዋቂዎች ሩጫ ውድድርን ማካሄዱን ትናገራለች። የቱሪዝም ሚኒስቴርም ዘንድሮ ይፋ ያደረገውን “ልወቅሽ ኢትዮጵያ” የአገር ውስጥ ቱሪዝምን የማስተዋወቅ ንቅናቄ ምክንያት በማድረግ አብሯቸው እየሰራ መሆኑን ትገልጻለች።

“ስፖርታዊ ውድድሮች ቢስፋፉ እግረ መንገድ ማህበረሰቡ አገሩን እንዲያውቅና የዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ፍሰት እንዲጨምር እድል ይከፍታል” የምትለው ዳግማዊት፤ ይህንን መሰረት በማድረግ ከቱሪዝም ሚኒስትር ጋር በመሆን በሀዋሳ ከሩጫው ባሻገር በታቦር ተራራ ላይ የእግር ጉዞ መደረጉን፣ የሃዋሳ ሃይቅን በደንብ በሚያሳይ ስፍራ ደግሞ ከነዋሪዎች ጋር የጋራ ባህላዊ ስርዓትን ያካተተ ትውውቅ ማድረግ መቻሉን ትገልፃለች። በውድድሩ ላይ የውጭ ጎብኚዎች፣ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ሶስት ሺህ አምስት መቶ የሚደርሱ ተሳታፊዎች እንደነበሩም ተናግራለች።

የቱሪዝም ዋናው ግብ ማህበረሰቡን በምጣኔ ሃብት መጥቀምን ጨምሮ የመስህብ ስፍራዎችን ማስተዋወቅና ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል ነው የምትለው ዳግማዊት፤ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያና ቱሪዝም ሚኒስቴር ባሳለፍነው ሳምንት በስፖርት ቱሪዝም ይህንን ልምምድ ለመፍጠር መንቀሳቀሳቸውን ትናገራለች። ከታላቁ ሩጫ ቀጥሎ በዓለም አቀፍ ውድድር የተመዘገበው የሀዋሳ የግማሽ ማራቶን ሩጫ መሆኑን ገልፃም የቱሪዝምን ፍሰት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመጨመርም ትልቅ ትርጉም እንደሚኖረው ትናገራለች።

“ለአስራ አንደኛ ጊዜ በተካሄደው የሀዋሳ ሩጫ ላይ የዴንማርክና የኖርዌይ አምባሳደሮች ተሳትፈው አገሪቱን በማህበራዊ ገፃቸው ለቀሪው የዓለም ክፍል አስተዋውቀዋል። የአሜሪካዋ አምባሳደር በቨርቹዋል ቴክኖሎጂ አዲስ አበባ ላይ ተሳትፋለች” የምትለው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ ዳግማዊት፤ ይህንን ልምድ ለማስፋት እየሰሩ መሆናቸውን ትገልፃለች። ከሚኒስቴር መስሪያቤቱ ጋር በጋራ በመሆን ወደ ሌሎችም አካባቢዎች ለማስፋትና የስፖርት ቱሪዝም ጽንሰ ሃሳብን ለማስተዋወቅ እንደሚሰራም ትናገራለች። ለአሁኑ ከቱሪዝም ሚኒስቴር ጋር ከሃዋሳ ቀጥሎ በበቆጂ ተመሳሳይ ሁነት እየተዘጋጀ እንደሆነም ጠቁማለች።

“የአገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት የስፖርት ቱሪዝምን መሰረት አድርገን የምናዘጋጃቸው ሁነቶች ወሳኝ ናቸው” የምትለው ዳግማዊት እንደ ታላቁ ሩጫ የሀዋሳን ውድድር “የሀዋሳ ሃይቅ” (lake hawassa) በሚል አዲስ ስያሜ የሲዳማንና የከተማዋን አጠቃላይ የመስህብ ሃብቶች በሚያስተዋውቅና ለማህበረሰቡ ቀጥታ የምጣኔ ሃብት ጠቀሜታን በሚሰጥ አግባብ ለማዘጋጀት እቅድ መያዛቸውን ጠቁማለች። በተመሳሳይ በበቆጂ በቀጣዩ ግንቦት ወር ላይ ተመሳሳይ ውድድር እንደሚያዘጋጅም ነው ያስታወቀችው።

የሀዋሳን የሩጫ ስያሜ መቀየር ያስፈለገው ዓለም አቀፍ ቱሪስቱ በከተማዋና በዙሪያዋ ያለውን ሃይቅ እንዲያውቅና በዚያውም የጉብኝት እቅድ ይዞ ቆይታውን እንዲያራዝም እድል ስለሚፈጥር ነው የሚል ሃሳብ የሰጠችው ዳግማዊት፤ በደቡብ አፍሪካ ቱ ኦሽንስ ማራቶን /“Two Oceans Marathon” /የሚል ስያሜ ውድድር የአገሪቱን የቱሪዝም መስህብ ለማስተዋወቅ ባለመ መልኩ እንደሚካሄድ በተመሳሳይ በዚምባቡዌ ቪክቶሪያ ፎልስ ማራቶን /“Victoria Falls Marathon” /መኖሩ በምሳሌነት በማንሳት ይህን መሰል የስፖርት ቱሪዝም በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፋፋት እየተሰራ መሆኑን ጠቁማለች።

“ቱሪዝም ሁነቶችን በማዘጋጀትና በማስተዋወቅ “ወቅት መፍጠር” ነው የምትለው የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ፤ የካቲትን በምሳሌነት አንስታ በሀዋሳ በየዓመቱ ይህን ወቅት መፍጠር ከተቻለና ይህንን ልምድ በሁሉም ክልሎች በመውሰድ በተለያዩ ጊዜያት የሚካሄዱ ስፖርታዊ ሁነቶችና ወቅቶችን በማስተዋወቅ ዓመቱን ሙሉ የማያቋርጥ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴ መፍጠር ይቻላል የሚል እምነት አላት። የታላቁ ሩጫም በዚህ ዙሪያ የበኩሉን እንደሚወጣም ተናግራለች።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የመተማ ጦርነት እና አጼ ዮሐንስ

**ዋስልኝ አየለ**



ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ አገራት ጋር ጦርነት አድርጋ አሸንፋለች:: በቅርቡም የዓድዋን እና የሶማሊያን ወረራ ያከሸፈችበት የካራማራ ድሎች ተከብረዋል:: እነሆ በመጋቢት ወር መጀመሪያ ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ዮሐንስ 4ኛ ሕይወታቸውን ያጡበትን የመተማ ጦርነት እናስታውሳለን::

እነሆ ከ134 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት አንድ እና መጋቢት ሁለት የመተማ ጦርነት እና የአጼ ዮሐንስ 4ኛ ሞት በኢትዮጵያ ውስጥ ተከሰቱ:: «ደርቡሽ» በመባል የሚታወቁት የሱዳን መሀዲስቶች የኢትዮጵያን ድንበር ጥሰው ጦርነት ከፈቱ:: ይህም ጦርነት በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለነበሩት ለአጼ ዮሐንስ አራተኛ መሰዋት ምክንያት የሆነው የመተማው ጦርነት ተባለ፤ ታሪኩም በዚህ ሳምንት መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም የተከሰተ ነበር:: በነጋታው መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም ደግሞ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም በተካሄደው የመተማ ጦርነት በጽኑ ቆስለው የነበሩት ንጉሰ ነገሥት አጼ ዮሐንስ 4ኛ አረፉ::

በመጀመሪያ «አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት» የተሰኘውን የተክለጻድቅ መኩሪያ መጽሐፍ ዋቢ አድርገን ታሪኩን በአጭሩ እናስታውስ::

ከጣሊያን ጋር ጦርነት ላይ የነበሩት አጼ ዮሐንስ አራተኛ ደርቡሾች ኢትዮጵያ ላይ ያደረሱትን ጥፋት ለመበቀልና የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር የደርቡሾችን ጦር ለሚመራው ዘኪ ቱማል «መጣሁ ጠብቀኝ! እንደ ሌባ አዘናግቶ ወጋኝ እንዳትል!» የሚል መልዕክት ላኩበት:: አጼ ዮሐንስ አራተኛ ይህን መልዕክት ልከው ጦራቸውን ይዘው ወደ መተማ ሄዱ::

በዕለተ ቅዳሜ መጋቢት 1 ቀን 1881 ዓ.ም ረፋድ አካባቢ ጦርነቱ ተጀመረ:: አጼ ዮሐንስ ልክ እንደ ተራው ወታደር መሐል ገብተው ሲዋጉ ዋሉ:: ኢትዮጵያውያን ጠንክረው እየተዋጉና ምርኮኛ እየያዙ ሳሉ አንዲት ተባራሪ ጥይት የንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ አራተኛ ደረት ላይ አረፈች:: የንጉሡን መቁሰል ያየው ሠራዊታቸውም መደናገጥና መሸሽ ጀመረ::

በጽኑ ቆስለው የነበሩት አጼ ዮሐንስ አራተኛ በማግስቱ መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም አረፉ:: ደርቡሾችም እየተከታተሉ የአጼ ዮሐንስ አራተኛን አስክሬን ይዘው፤ አትባራ ወንዝ ላይ የነበሩ የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት አድርሰው፣ መጋቢት 3 ቀን 1881 ዓ.ም የአጼ ዮሐንስ አራተኛን ጭንቅላት ወሰዱ::

የአጼ ዮሐንስ አራተኛ መልዕክት፤ ለዘኪ ቱማል እንደደረሰ በደርቡሾች ዘንድ ሽብር ተፈጥሮ ነበር:: ዘኪ ቱልማ ወታደሮቹን ሰብስቦ «ምን ይሻለናል? ውጭ ወጥተን ሜዳ ላይ እንጠብቃቸው ወይስ እዚህ በቅጽሩ ውስጥ ምሽግ ውስጥ እንጠብቃቸው?» ብሎ ሲጠይቅ፤ አህመድ አሊ የሚባለው (የእስላሞች ቃዲ ይሉታል የታሪክ ጸሐፊው ተክለጻድቅ መኩሪያ) «አይ! ሜዳ ላይ ከወጣን አበሾች ፈረሰኞች ናቸው፤ በፈረስ አጎዳ ይጥሉናል፣ ስለዚህ እዚሁ አጥራችን ውስጥ ሆነን ብንጠብቃቸው ይሻለናል» ብሎ እንደነበር የታሪክ መጻሕፍት ይናገራሉ::

ደጃዝማች ካሣ ምርጫ (አባ በዝብዝ ካሳ) አጼ ተክለጊዮርጊስን ድል ካደረጉ በኋላ «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ግርማዊ ዮሐንስ ራብዓዊ ስዩመ እግዚአብሔር ንጉሰ ፅዮን ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» ተብለው ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም ነገሱ::

አጼ ዮሐንስ 4ኛ የተንቤንና የእንደርታ ባላባቶች ከነበሩት ወላጆቻቸው ሐምሌ 5 ቀን 1825 ዓ.ም ማይ በሀ (ተምቤን) በሚባል ሥፍራ ነው የተወለዱ። ከመንገሣቸው በፊትም «ርዕሰ መኳንንት ደጃዝማች በዝብዝ ካሳ» በመባል ይታወቁ ነበር። በወቅቱም በትግራይ መኳንንት እግር ተተክተው የአካባቢው ገዢ ሆነው ቆይተዋል።

በሰሜን በኩል በወደቡ አቅራቢያ መገኘታቸውም ከአውሮፓውያን ቆንሲሎች ጋር ወዳጅነት እየመሰረቱ መጠነኛ የትጥቅ ድጋፍ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል:: ደጃዝማች ካሳ ምርጫ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥት እንደሚሆኑ እርግጠኛ ስለነበሩ «ደጃዝማች» ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ራሳቸውን ለውጭ አገራት መንግስታት በደብዳቤ ያስተዋውቁ ነበር።

ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ከሞቱ በኋላ ለሦስት ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የነበሩት አፄ ተክለጊዮርጊሥ፣ ደጃዝማች ካሳን ሊያስፈራሩ አንድ ስልቻ ጤፍ አስቋጥረው «የሰራዊቴ ቁጥር እንደዚህ የበዛ ነውና አትችለኝም፤ ስለዚህ ገብር!» ብለው ላኩባቸው:: ደጃዝማች ካሳ ደግሞ በምላሹ የተላከውን ጤፍ አስቆልተው «የእኔ ሰራዊት ደግሞ ያንተን ሰራዊት እንደዚህ ይቆላዋል» ብለው ላኩላቸው:: የተናገሩት አልቀረም፤ ደጃዝማች ካሣ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ዓድዋ አካባቢ አሰም በሚባል ሥፍራ ላይ ሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም ወግተው ድል አደረጓቸው::

ከድሉ በኋላም ለበዓለ ንግስናቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲያደራጁ ቆይተው ጥር 13 ቀን 1864 ዓ.ም በእለተ እሁድ በአክሱም ፅዮን ቤተ ክርስትያን በጳጳሱ አቡነ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ግርማዊ ዮሐንስ ራብዓዊ ስዩመ እግዚአብሔር ንጉሰ ፅዮን ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ» ተብለው ነው የነገሡ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለአገራቸውና ለሃይማኖታቸው ባላቸው ቀናኢነት የሚታወቁት አጼ ዮሐንስ 4ኛ፣ አንዲት ጠንካራ አገር እውን እንድትሆን ያለ ዕረፍት ሲተጉ ኖረዋል። በተለያዩ አቅጣጫዎች አገር ለመውረር ከመጡት ከግብጾች፣ ከቱርኮች፣ ከጣሊያኖችና ከደርቡሾች (መሐዲስቶች) እና ከሌሎች የውጭ ኃይሎች ጋር ተደጋጋሚ ጦርነቶችን አድርገው ነፃ አገርን ለቀጣዩ ትውልድ ያስረከቡ ትጉህ ንጉሥ እንደሆኑ የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ::

አጼ ዮሐንስ አራተኛን በብዙዎች ዘንድ እንዲታወቁ ያደረጋቸው ይሄው በዚህ ሳምንት የምናስተውሰው የመተማው ጦርነት ነው::

አጼ ዮሐንስ 4ኛ ገላባትን፣ ብሎም አምድሩማንንና ካርቱምን በመያዝ የደርቡሽን መንግሥት ለመገርሰስ ዝግጅት መጀመራቸው ሱዳን ውስጥ ጭምጭምታ እንደተሰማ፤ አጼ ዮሐንስ በዋነኞቹ የጦር መሪዎች በእነ ራስ አርአያ ድምፁ፣ ራስ ሚካኤል (መሐመድ አሊ)፣ ራስ ኃይለማርያም ጉግሳ፣ ራስ አሉላ፣ ስልሕ ሻንቆ እና ሌሎችም ታላላቅ የጦር አዛዦች የሚንቀሳቀሱ ክፍለ ሠራዊቶችን በመምራት በቅድሚያ ገላባትን ለመያዝ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸው ጭምር በደርቡሽ ዘንድ ተሰማ።

የገላባቱ ምሽግ ዋና አዛዥ ሸክ በኪ ጡማል በመምጣት ላይ ያለውን ጠላት ከምሽግ ውስጥ ሆኖ መዋጋት ወይስ ገና ከመንገድ ላይ መቁረጥ የትኛው እንደሚሻል አማካሪዎቹን አወያየ። ካለምንም ማወላወል ምሽጋቸውን ማጠናከር አማራጭ የሌለው ዘዴ መሆኑ እርግጥ ነበር። እንደማዕበል የሚነጉደውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ከምሽግ ወጥቶ መመካት የማይታሰብም የማይሞከርም ነበር።

አጼ ዮሐንስን ለመግጠም የተመደበው የዘኪ ጥምር ጦር 80 ሺህ ደርሷል። ከቁጥሩ በላይ ጦሩ ምሽጉን አጥብቆ በመያዝ የመጣበትን ጦር ለመመከት ቁርጠኛ ነበር። አዋጅ ነጋሪዎች በገጠር በከተማው እየዞሩ ሱዳናዊ ሁሉ የዕለት ተግባሩን ትቶ ጠብመንጃውን አንግቶ፣ ጎራዴውን ታጥቆ አገሩን እንዲከላከል የመሪያቸውን ትዕዛዝ አሰሙ። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት የዘመቻ ዝግጅት ከተነገረው በላይ ተጠናክሮ መቀጠሉን የደርቡሽ ወታደራዊ ምንጮች ገለፁ። እነዚህ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት መረጃዎችን ያሰባሰቡ የነበሩ ሰላዮች የኢትዮጵያን ሠራዊት እንቅስቃሴ በሚከተለው መልክ አቀረቡት።

«የሀበሻ ሠራዊት እንደሰማይ ከዋክብት እንደባህር አሸዋ ህልቆ መስፈርት የለውም። ሠራዊቱ ሲርመሰመስ ለዓይን እይታ የሚታክት፣ መጨረሻው ከአድማስ ባሻገር የሆነ፣ የዘመቻው ንቅናቄ በሚያስነሳው ምድራዊ ደመና ጸሐይን ያጠቆረ አስፈሪ ኃይል ነው»

ይህ ደማቅ ወታደራዊ ዘገባ የደርቡሾች ዋና ከተማ የነበረችውን አምድሩማንን ከወዲህ ወዲያ በሽብር አናወጣት። ከዕለታት አንድ ቀን ሱዳን በሀበሻ እንደምትተፋ፣ የንጉሡ ፈረስም ኮቴው በፈሰሰው ደም ተውጦ፣ እንደ ወሬ ነጋሪ ከጥፋት በተረፈችው አንዲት ዛፍ ጥግ ታስሮ እንደሚታይ እንደ ትንቢት የሚነገረው አፈ ታሪክ ጊዜው መድረሱና ትንቢት የተነገረለት የሀበሻ ንጉሥ ዮሐንስ እንደሆነ ትንቢት ተናጋሪዎች አስረዱ።

በ1881 ዓ.ም ወርሃ የካቲት መጨረሻ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስ 4ኛ ጎንደር ከተማን ለቅቀው በመውጣት ሕዝብን ለማጥፋት የተነሳውን ቁርጠኛ ጠላት ለመደምሰስ ሠራዊታቸውን በረድፍ በረድፍ አስከትለው ወደ ገላባት ተመሙ። ከከተማዋ አቅራቢያ እንደደረሱ አጼ ዮሐንስ እንዲህ አሉ::

«እንደ ሌባ ተሸሎክልኮ መጣ እንዳትለኝ፤ ለፍልሚያው ተነስቻለሁና ተነስ!» ብለው ለደርቡሹ አዋጊና የጦር አዛዥ መልዕክት ሰደዱለት:: ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ከወንዶቹ ሌላ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወይዛዝርት አብረው ተሰልፈዋል። እነዚህ ሴት ዘማቾች የትዳር ጓደኞቻቸውን፣ የእጮኞቻቸውን፣ የወንድሞቻቸውንና የአባቶቻቸውን የሞትና የመከራ ጽዋ ለመቅመስ ኑሯቸውን በትነው፣ ጎጇቸውን ዘግተው ወደ ጦር ሜዳ የዘመቱ ናቸው።

አጼ ዮሐንስ በቀጥታ ወደ ውጊያው ሲገቡ፤ ሠራዊታቸው መሪውን እየተከተለ ከምሽጉ ውስጥ በፉከራና በቀረርቶ እየዘለለ ገባ። ከጦር አውድማው የሚነሳውን አቧራ አውሎ ነፋሱ ሲያነሳው እሽክርክሪት እየሰራ በውጊያው መሀል ሰይጣናዊ ጭፈራውን አቀለጠው። ከወዲያም ከወዲህም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ለዘመን ፍጻሜ የሚዋደቁ የሚመስሉ ወታደሮች አንዱ ሌላውን ለመለየት በማይቻልበት ሁኔታ የሞትና ሽረት ትግሉ የቀኑን ብርሃን ጽልመት አለበሰው።

ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ ጦርነቱ መሐል ገብተው ሲዋጉ ያየው የኢትዮጵያ ወታደር መንፈሱ በአንዳች ወኔ እየተፈነቀለ ግስጋሴውን ቀጠለ። የደርቡሾች ጠንካራ ምሽግ መላላትና መሳሳት ጀመረ።

ከደርቡሾች ሰይፍና የጥይት አረር ይልቅ የኢትዮጵያ ጦር የከበደው ነገር በአገር ምድሩ የበቀለው እሾህማ ጥቅጥቅ የቆላ ግራር ነበር። ለደርቡሾች ተደራቢ ምሽግ ሆነላቸው። ሀበሾቹ ግራሩን ግራ ቀኝ ረግጠው እየዘለሉ፣ አንዳንድ ጊዜም እያቃጠሉ ወደ ዋናው የደርቡሽ ማዘዣ ጣቢያ ዘልቀው ለመግባት ሲዋጉ የደርቡሽ ሠራዊት አጋጣሚውን በመጠቀም ጥይቱን አርከፈከፈው። በዚህ የትንቅንቅ ሰዓት ነበር ከማህዲ ሰፈር አምልጠው ለኢትዮጵያ ሠራዊት እጃቸውን የሰጡ ትኹሪሮች (ደቡብ ሱዳናውያን) ጠቃሚ መረጃ የሰጡት።

በደርቡሾች የጦር ሰፈር ደካማው የውጊያ ግንባር ያለበትን ምርኮኞቹ ተናገሩ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ለመጨረሻው የሞት ሽረት ድል ወጊያውን አፋፋመ::

በሁለቱም ወገን ከተከፈለ ከባድ የሕይወት መስዋዕትነት በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ውቅያኖስ ማዕበል እያስገመገመ ከፊት ለፊቱ የቆመውን ሁሉ እየደመሰሰ የደርቡሾችን ወታደራዊ እምብርት ዘልቆ በመግባት የበላይነቱን ተቀዳጀ። ድልን ጨብጦ በመገስገስ ላይ የነበረውን ኃይል በተመለከቱ ጊዜ ከኋላ ሆነው ግፋ በለው እያሉ እልል ሲሉ የዋሉት በሺዎች የሚቆጠሩ የደርቡሽ ሴቶች ልብ የሚነካ እዬዬና ዋይታ ያሰሙ ጀመር።

የኢትዮጵያ ጦር አሁንም ማጥቃቱን በመቀጠልና ያገኘውን ድል በማጠናከር የደርቡሾችን ምሽግ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ይህ ግስጋሴ ሀበሾችን ወደ ፍፁም ድል በር የሚያደርሰው ወሳኝ እርምጃ ነበር።

የገላባት (መተማ) ጦርነት ከዚያም ከዚህም የሰው ልጅ እንደ ቅጠል ቢረግፍበትም ድል ፊቷን ወደ ዮሐንስ ማዞሯ አጠራጣሪ አልነበረም። ሐበሾች የደርቡሽን የትጥቅና የስንቅ ማከፋፈያ ማዕከልን ተቆጣጠሩ። የጦር አዛዡ አቡ አንጋ ጦርነቱን ይመራ የነበረው ከዚሁ ሠፈር ሆኖ ነበርና የዮሐንስ ወታደሮች የማዘዣ ጣቢያው መደምሰስን ተከትሎ የደርቡሾችን የሬሳና የቁስለኛ ክምር በማገላበጥ የራሱን የአቡ አንጋን አስክሬን ለማግኘት ፍለጋ ጀመሩ።

ከማዘዣ ጣቢያቸው ሙሉ በሙሉ መደምሰስና ትጥቅና ስንቃቸው በኢትዮጵያ ሰራዊት መማረክ በኋላ የደርቡሾች ወኔ ሚሸሸ። የደርቡሽ ጦር በእጁ የያዘው ጥይትና ሌላ አስፈላጊ የውጊያ መሣሪያ አልቆ መዋጋት በማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ የዮሐንስ ዘማች ኃይል አሸናፊነት እርግጥ ሆነ።

ደርቡሾች ተሸንፈው እግሬ አውጭኝ እያሉ በሚሸሹበት ሰዓት ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ በአንዲት ጥይት ተመትተው መውደቃቸው በኢትዮጵያውያን ሰፈር ተሰማ። ወሬው እየተቀጣጠለ ጦሩን ግራ አጋባው:: በደርቡሽ ቆራጥነት ያልተፈቱት ሀበሾች በድል አፋፍ ላይ ቆመው የደርቡሽን ሽሽት አሻግረው በሚመለከቱበት ሰዓት በንጉሠ ነገሥታቸው መመታት ድንጋጤ ጥርጣሬና ተስፋ መቁረጥ ወረራቸው:: ከድል በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ በተተኮሰችው ጥይት ምክንያት የኢትዮጵያውያኑ ሠፈር ተስፋ መቁረጥና ትካዜ ገባበት። ካለ መሪ ካለ አስተባባሪ የቀረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ፊቱን ወደ አገሩ በማዞር ጉዞ ጀመረ። ድል ፊቷን ወደ ኢትዮጵያውያን ብታዞርም እንደገና ወደ ደርቡሽ ዞረች::

የተበታተኑት የደርቡሽ ሠራዊቶች እየተሰበሰቡ ወደ ተደመሰሰው ምሽጋቸው መመለስ ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ድል የቀናው የደርቡሽ ሠራዊት የአጼ ዮሐንስ አራተኛን ራስ ቆርጦ ለመውሰድ ዕድል አገኘ::

የአፄ ዮሐንስ ራስ በአምድሩማን አደባባይ ለዕይታ ቀርቦ እንደበቃ በቆዳ ተለብዶ ወደ ደንጎላ (ዳርፉር ግዛት) ከዚያም አልፎ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ በግመል ተጭኖ እንዲወሰድ ተደርጓል:: እነሆ ዛሬ ድረስ ይህ ታሪክ በጠላትም ሆነ በወዳጅ ወገን ይነገራል::

አጼ ዮሐንስ 4ኛ ከነገሥታቱ ለየት የሚያደርጋቸውም ይህ ታሪካቸው ነው:: ንጉሥ ሆነው ልክ እንደ ተራ ወታደር ሲዋጉ ነው የሞቱት:: እንደ አገር ባላቸው ታሪክ ደግሞ ኢትዮጵያ አገራቸውን የማያስደፍሩ ጀግኖች አገር መሆኗን አሳይተዋል:: የጀግኖችን ታሪክ የምናስታውሰውም ለዚህ ነው::

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## የቃቄ ውርድወት

ሙሉጌታ ብርሃኑ



በዚያን ዘመን..ለመሆኑ በየትኛው ዘመን?..ዘመኑን የሚወክል አሀዛዊ ቁጥር ስለሌለ ዝም ብሎ በዚያን ዘመን ማለቱ ይሻላል። እናም በዚያ ዘመን ሴትነትም ሆነ የሴቶች መብት ከትልቅ ዋርካ ስር እንደምትገኝ አበባ ነበረች። ዋርካው ካልራራላት በቀር ጸሃይም ሆነ ዝናብ ማግኘት ብርቋ ነው። እንደ ዛሬው የሴቶች መብት እያልን አቤት የምንልበት ፍርድ ቤትም ሆነ የሚሰማ ዳኛ ያልነበረበት ዘመን። እንዲያውም ከነጭራሹ የሴቶች መብት የምትለው ሀረግም አልተፈጠረችም ነበር። ነገር ግን በአንድ ወቅት፣ ከዛሬ መቶ ሰላሳ ዓመታት በፊት የሴትነት መብት ባንዲራ ይዛ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ብልጭ ብላ የጠፋች አንዲት ሴት ብቅ ብላ ነበር። የሴትነት ቁንጮ የጀግንነት ተምሳሌት እሷም የቃቄ ውርድወት ናት።

የቃቄ ውርድወት ተወልዳ ያደገችው በዛሬዋ የጉራጌ ዞን የምሁር አክሊል ወረዳ ውስጥ ነበር። መቼም በአይኑ ያያት ሁሉ ስለ ጀግንነትዋ ብቻ ሳይሆን ስለ መልካምነቷና ምትሃታዊ ውበቷም ጭምር ሳያደንቅ አያልፍም። ውርድወትን ቆንጆ ናት ከማለቱ ይልቅ ውበት ስጋ ለብሶ የተገለጠባት ሴት ናት ማለቱ ይቀላል። በቤተሰቦችዋ እንደ አይን ብሌን የምትታይና በወንድም እህቶቿ ተከባ በእንክብካቤ ያደገች ነበረች። የቃቄ ውርድወት እየተባለች ብትጠራም የእሷ ስም ግን ውርድወት ነው። የቃቄ ደግሞ የወላጅ አባቷ ስም ነው። ውርድወት ከልጅነቷ ጀምሮ ያለ እድሜዋ ጀብዱ መስራት የሚያስደስታት ሴት ነበረች።

ውርድወት ወደ ሴቶች መብት ተሟጋችነት እንድትገባ የገፋፋት አንድ ምክንያት ነበራት። በልጅነት አስተዳደጓ እንደሌሎቹ የአካባቢዋ ሴቶች ችግር የሚባለውን ነገር እምብዛም አታውቀውም። ምክንያቱ ደግሞ በእንክብካቤ ያደገች የባለአባት ልጅ ናትና። ታዲያ ይህችን ቆንጆ ልዕልት የራሱ ለማድረግ የአባቷን ደጅ ያልረገጠ ወንድ አነበረም። ስለ እርሷ ውበት የሰማ በሙሉ እድሌን ልሞክር በማለት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ዘመኑ ደግሞ ዘመድ ከዘመዱ፣ አህያም ከአመዱ ነበርና የወላጆቿ ምርጫ ሆኖ እንደ እነርሱ ባለጠጋ ለነበረ ለአንድ ባለአባት ልጅ ዳሯት። በድሮው ዘመን በአገራችን በተለይ ደግሞ በጉራጌ ማህበረሰብ ዘንድ ባለጠጋ የሆነ ወንድ የባለጠግነቱ ማሳያ በሀብትና ንብረቱ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በሚስቶቹም ቁጥር ጭምር ነው። እንግዲህ ብዙ ያለው ብዙ ያገባል ማለት ነው። ውርድወትም የገጠማት ከዚህ የተለየ አነበረም። የእኔ ነው ብላ ቤቱ የገባችለት ሰው፣ የእሷ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሴቶች ባል ነበር። ይህ ጉዳይ ውርድወትን ይቆረቁራትና ምቾት ይነሳት ነበር። በትዳር ሕይወቷ ቀናትን እያስቆጠረች በመጣች ቁጥር እልህ የታከለበት ቁጣና ንዴት እየንተከለከለ ከውስጧ መገንፈል ጀመረ። እናም በደልን በጸጋ ተቀብሎ መኖር አልሆንላት አለና አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባት ወሰነች። ነገሩን በሀሳቧ ማውጠንጠንና እለት ከእለት ለብቻዋ መብሰልሰሉን ተያያዘችው። በመጨረሻም አንድ ሀሳብ ከአዕምሮዋ ከተፍ አለላት።

ሀሳቧን ከግብ ለማድረስና ብዙ ሴቶችን ከተጫነባቸው የጭቆና ቀንበር ለማላቀቅ በቀየሰችው መንገድ መሰረት የትግል ጉዞዋን ጀመረች። በመጀመሪያም ጎረቤቷ ከነበሩ ሴቶች ዘንድ በመሄድ ስለ ጉዳዩ አማከረቻቸው። ብዙ ሴቶችም ሀሳቧን በመደገፍ ይህንን ትግል በመደገፍ ሊቀላቀሏት ፈቃደኛ ሆኑ። ውስጥ ለውስጥ በነበራቸው ቅስቀሳም ቁጥራቸው እየተበራከተ ሄደ። አንድ ቀን ውርድወት ሴቶቹን ሁሉ በመሰብሰብ ይህንን ንግግር አደረገችላቸው፣ ‹‹ወንዶቹ ቀን ቀን በጀፎሮ (በቤተ-ጉራጌ አውራ መንገዶች) በሚገኙ ዋርካዎች ስር ሆነው ሲወያዩ፣ ገበጣና የተለያዩ ጨዋታዎች በመያዝ እንዳሻቸው እየተዝናኑ ውለው ማታ ይገባሉ፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የፈለጉትንና ሀብት ንብረታቸው የሚፈቅደውን ያህል ሴት ያገባሉ፡፡ ባሎቻችን ቢናፍቁን እንኳን እነርሱ ፈልገውን እስካልመጡ ድረስ መቼም አናገኛቸውም። እኛ ሴቶቹ ክብራችንን ገፈው እንደሚስት ሳይሆን እንደ እቃ በገንዘባቸው ይሸምቱናል..ለምን! ስለምንስ እንዲህ ይሆናል! ማግኘት ያለብንን የሴትነት ክብርና ወግ ስንነጠቅ በፍርሃት አንገት ደፍተን እስከመቼ እንኖራለን? ከዚህ በኋላ እያንዳንዳችን ከቤታችን በመጀመር ድምጻችንን አንድ አድርገን ይህንን የተጫነብንን ቀንበር ልንሰብር የግድ ነው!›› በዚህም ንግግራ የሴቶቹን የተኛ ልብ በወኔ ቀሰቀሰችው። ስብሰባውም በውስጥ እየተደጋገመና በቁጥርም ሆነ በስነልቦና ከንዳቸው እየጠነከረ መጣ።

የሚስቶቻቸው ባህሪ ከጊዜ ወደጊዜ እየተቀየረና እየጠጠረ የመጣባቸው ባሎች በሁኔታው ግራ በመጋባት መጨነቅ ጀመሩ። ሴቶቹ ከነበራቸው ድብቅ ስብሰባና ውስጣዊ ፍርሃት በመውጣት የራሳቸውን ነጻነት አውጀው በጀፎሮ ላይ መሰብሰብ ቀጠሉ። በማህበረሰቡ ባህል ሴቶች በአደባባይ ላይ ከተሰበሰቡ እንደ ነውር ይታያል። ይህን ጥሰው በአደባባይ በመሰብሰባቸው ምን ጉድ መጣብን ሲሉ ወንዶቹ እርስ በእርስ በጥያቄ ፊት መተያየት ጀመሩ። ነገሩም አላማረቸውምና አንዳች ነገር እየዶለቱ እንደሆነም ጠረጠሩ። በአንደኛው የስብሰባ እለትም ወንዶቹ ወደ ቃቄ ውርድወት ባለቤትና የአካባቢው ሰብሳቢ ሆደሆነው ወደ አጋዝ ፍርችየ ዘንድ በመሄድ በባለቤቱ መሪነት እየተካሄደ ያለውን የሴቶቹን ጉዳይ በሸንጎ ይጠይቅላቸው ዘንድ አወጉት።

አጋዝ ፋርችየም ይሄድና ሴቶቹን ‹‹ምንድነው?›› ይላቸዋል፡፡ እነርሱም መልሰው ‹‹ምንድነው?›› ይሉታል፡ ፡ ‹‹ሴት ልጅ በጀፎረ መሰብሰብ ነውር ነውና አይቻልም›› ይላቸዋል፡፡ እነሱም ‹‹የሚያሰባስበን ጉዳይ ስለገጠመን እንሰባሰባለን›› ብለው ይመልሱለታል፡፡ ጀግናው ፋርችየ እዚህ ላይ ፈተና ገጠመው፡፡ በጣም የሚወዳት እልኸኛ ሚስቱን ውርድወትን ፊት ቢመለከት ፈጽሞ ሌላ ሆነችበት። ስልጣኑን እንኳን ሳይፈሩ የሚሞግቱት የሴቶቹ ሁኔታ ያስደነገጠው ፍርችየም ፈራ ተባ እያለ በእርጋታ ‹‹እሺ አሁን ጉዳያችሁ ምንድነው?›› ሲል ደግሞ ጠየቃቸው። ሴቶቹም ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች እንዲስተካከልላቸው እንዲህ በማለት ጠየቁ። ‹‹አንደኛ እናንተ እንዳሻቹ፣ ባሻችሁ ጊዜና ቦታ ስትዝናኑ ውላችሁ ስትገቡ እኛ ደግሞ ቤታችንን ለማቅናት ደፋ ቀና ስንል ውሎ ይመሻል። በአንዲት ሴት ላይም ብዙ ሴት ታመጣላችሁ። ስለዚህ እኛ ሴቶችም የፈለግነውን የማግባት መብት ይሰጠን። ይህ ካልሆነ ደግሞ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ብቻ ይሁን። ሁለተኛ ወንድ እንጂ ሴት ልጅ ባሏን የመፍታት መብት ስለሌላት በደል እየደረሰባትም ችላ የግዷን ትኖራለች። ፍቺ ስትፈጽምም የምታልፈው መከራ ብዙ ነውና ለዚህም መፍትሄ እንፈልጋለን!›› በማለት የ'አንቄት' ህግ እንዲነሳላቸው ጠየቁ። 'አንቄት' በጉራጌ ማህበረሰብ የሰማንያ ውል እንደማለት ነው። በዚህ ልማዳዊ ህግ መሰረት አንዲት ሴት ባሏን ስትፈታ ባሏ ‹ፈትቼሻለሁና የወደደ ያግባሽ› በማለት ደጋግሞ ሶስት ጊዜ ሳይመርቃት በራስዋ ፈቃድ ጥላ የወጣች እንደሆን የተረገመችና ቀጣዩም ትዳርዋ ያልተባረከ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። ሴቶቹ በሶስተኛ ደረጃ ያነሱት ደግሞ ‹‹ሴቶች በጀፎሮ መሰብሰብ አለባቸው፤ ስለዚህ ክልከላው መቆም አለበት›› የሚል ነበር።

ነገሩን በዝርዝር የሰማው ፍርችየ ጉዳዩን ይዞ ወደ ወንዶቹ ዘንድ ተመለሰ። የሴቶቹ አመጽ እየጨመረ በመምጣቱ፣ ጉዳዩ ለወንዶቹ እረፍት የሚነሳ ነበርና በጋራ መከሩበት። አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለው ሀሳብ ደግሞ የሁሉንም ቤት ያንኳኳ አስጨናቂ ነጥብ ሆነባቸው። ከሁለትና ከሶስት ሚስት ጋር የተሳሰረው ወንድ ሁሉ ጉዱ ፈላበት። በዚህ ላይ የፍቺ ነጻነቱን ቢሰጧቸው በአንዴ ወደ አዘቀጥ ውስጥ መግባታቸው እንደማይቀር ገብቷቸዋል። የሴቶቹ ህብረት እየጠነከረ፣ ከአካባቢው እየወጣና እየተስፋፋ ሙሉ የሰባት ቤት ጉራጌን እያካለለ በመሆኑ፣ ይህን አመጽ በጉልበት መሞከር ደግሞ በእሳት ላይ ቤንዚን ማርከፍከፍ መስሎ ታያቸውና የሚዙት የሚጨብጡት ጠፋቸው።

በአካባቢው ሽማግሌዎች ተጀምሮ መቋጫ ያላገኘው የእነ ውርድወት ጉዳይ በቤተ-ጉራጌዎች የሽምግልና ስርዓት መሰረት ከአንዱ ወደ አንዱ፣ ደረጃ በደረጃ ከጎሳ ጠቅላላ ጉባኤ ወደ ኩታ ገጠም ጎሳዎች ጉባኤ፣ ከዚያም ወደ ጠቅላላ ቤተ-ጉራጌ ሸንጎ ወይም የኧጆካ ሸንጎ ወደሚሰኘው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ ወደሆነው ባህላዊ ምክር ቤት አመራ። በበሳልና ጠቢብ አባቶች የሚመራውና ምንም የማይፈታው ነገር የለም የተባለለት ይህ ሸንጎ ለመጀመሪያ ጊዜ እጅግ በጣም ፈታኝና ውስብስብ ጉዳይ ገጠመው። እንቆቅልሹን ለመፍታትም ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግና ጉዳዩን በጥልቀት በማጤን ከሶስት ጊዜ በላይ የተለያዩ ቀጠሮዎችን ቢሰጥም ለመፍታት ግን ከበደው። በቀጠሮ ብዛት የተሰላቹት ሴቶቹ አሁንም በአስቸኳይ ውሳኔ ይሰጠን ሲሉ ጩኸታቸውን ለሸንጎው አሰሙ። ሸንጎውም የውሳኔ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ አሰናበታቸው። በዚህ መሃል ታዲያ አደጋ ያንዣበበበት የሸንጎው አባላት ሴቶቹን በግል እያገኙ ይደልሏቸው ጀመር፡፡ ሴቶቹ ግን ወይ ፍንክች! አሉ። የጀርባ አጥንታቸው የነበረችው ውርድወት ደግሞ ‹‹ገላችሁ አፈር አልብሱኝ እንጂ በሕይወት እያለሁ ፈጽሞ አልተወውም›› በማለት የቆራጥነቷን ጥግ አሳየቻቸው። ውርድወትን ማሸነፍ ጉዳዩን በድል እንደማጠናቀቅ ነውና ሸንጎውን በዝግ በማድረግ እሷን መርቻ መንገድ ማሰስ ጀመሩ። የአንቂት ስርዓትን ለእሷ ብቻ እናንሳላት በሚል ሀሳብ ግማሹ ቢስማማም ባለቤቷ ፍርችየ በጣም የሚፈራ ሰው እንደመሆኑ ከፊሉ እንዴትስ ተብሎ በእሱ ላይ መወሰን ይቻላል ሲሉ ሞገቱ። በስተመጨረሻም ባሏን ፍርችየን ለመማጸን ወስነው ሄዱ። እሱን ማሳመንም ቀላል አልነበረምና ከብዙ ልፋት በኋላ ለሚስቱ ውርድወት የአንቂት ስርዓትን ለማንሳት ተስማማ። ይህ ለሸንጎው ትልቅ እፎይታን የፈጠረ ጉዳይ ነበር። ከዚህ በመቀጠልም ወንዶቹ አንድ ሚስጥራዊ ስብሰባ አደረጉ። ውሳኔ የሚሰጥበት ቀን ታውቆ ስለነበረ በዚህ እለት የትኛዋም ሴት ወደ ሸንጎ እንዳትመጣ ወንዱ ቢችል አባብሎ አሊያም አስገድዶ ከቤት እንዲያስቀራት ተባለ።

የዚያን ሰሞን ወንዶች ለሚስቶቻቸው የሚያሳዩት ፍቅርና እንክብካቤ ልዩ ነበር። አንዳንዶቹ የእንሰት ተክሎች፣ ላሞች፣ በግና ፍየሎች በጉቦነት ለሚስቶች ሽልማት እየተባሉ ተሰጡ፡፡ ወንዶቹ ትልቁ ጥረታቸው የቀጠሮውን ጉዳይ እንዲሰርዙና ሀሳቡንም እንዲረሱት ነበር። ጥቂቶቹም ተሳካላቸውና የሚስቶቻቸውን ሀሳብ ማስለወጥ ቻሉ። አንዳንዶቹም ቢሆኑ ከባሎቻቸው በደረሰባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ነገም ሌላ ቀን ሲሉ ለጊዜው ለመተው ወሰኑ። የቀጠሮው እለት ሽማግሌዎቹ በጠዋቱ ቦታ ቦታቸውን ይዘው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

ውርድወት ፊቷ እንደጠዋት ጮራ እያበራ ከጃንጥላዋ ስር በሰጋር በቅሎዋ ስትከንፍ ደረሰች። ከስፍራው ቁጭ ብላ ሴቶቹን በጉጉት እየጠበቀች ደቂቃዎች እየነጎዱ ሰዓቱ ሄደ። በጣም እየተበሳጨች ሄዳ ከበቅሎዋ በመቀመጥ ወደከፍታ ቦታ ወጥታ ይመጡ እንደሆን ብላ ከእሩቅ ብትመለከት ዝር የሚልም የለም። ተመልሳ ሽማግሌዎቹ ጋር በመምጣት ሌላ ቀጠሮ እንዲሰጧት ብጠይቅም አውቀው ነገሩን ያበላሹት እራሳቸው ናቸውና የማይሆን ነው ሲሉ እምቢ አሏት። ሴቶቹ ሁሉ ትዳራቸውን መርጠዋልና አንቺም ሂጂ ቢሏት፤ እሷ ግን አይሆንም ሴቶቹ ሁሉ ባሎቻቸውን ፈርተው አሊያም ተታለው ቢቀሩም እኔ ለራሴ አለሁና ፍርድ እንድትሰጡኝ ብላ በግትር አቀማ ፀናች፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹም አማራጭ አልነበራቸውምና የአንቂት ስርዓትን አነሱላት። የቃቄ ወርድወት የራስዋን መብት በማስከበርዋ ደስ ቢላትም፤ ሴቶቹን ሁሉ ነጻ የማውጣት ትግሏ በተለያዩ ሴራዎች በመፍረሱ እያዘነች ተመለሰች። ከዚህ በኋላም ወደ አባትዋ ቤት ተመልሳ የራሷን ኑሮ ቀጠለች። በሰራችው ስራም ስሟ ከአካባቢዋ አልፎ በአገሪቱ ሁሉ ናኘ። ህልሟ በጊዜው ባይሳካም በትንሹም ቢሆን የሴቶቹን አይን አብርታለችና ብዙ ነገሮችም እየተለወጡ መጡ። ፈር ቀዳጅ በሆነው የሰለጠነ አስተሳሰብና ተግባሯ ባለትልቅ አዕምሮ ሴት ናትና በዚህ ሳምንት በተከበረው የሴቶች ቀን ልትመሰገን ይገባታል።

# ዓለም አቀፍ

## ሺ ጂንፒንግ ለሦስተኛ ዘመን የቻይና ፕሬዚዳንት በመሆን ቃለ መሐላ ፈጸሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቻይናው መሪ ሺ ጂንፒንግ ለሦስተኛ ዙር አገሪቱን ለመምራት ቃለ መሐላ ፈጸሙ።

ሺ የሕይወት ዘመን መሪ ቢሆኑም በደንቡ መሠረት የቻይና የተወካዮች ምክር ቤት በሚባለው አዳራሽ ተገኝተው ቃለ መሐላ ፈጽመዋል።

የ69 ዓመቱ ሺ በቻይና ታሪክ ከፍተኛ ሥልጣንና የፖለቲካ ቁጥጥር ካላቸው መሪዎች ተርታ ይመደባሉ።

በቻይና መንግሥት መዋቅር ከፍተኛው ሥልጣን የሚመነጨው ከፓርቲው ነው።

የእርሳቸው ከፍተኛው የሥልጣን እርከንና ቁጥጥርም ከፕሬዚዳንትነት ይልቅ የኮሚኒስት ፓርቲው ዋና ጸሐፊ እንዲሁም የማዕከላዊ ወታደራዊ ኮሚሽን (CMC) ሊቀመንበር ከመሆናቸው ላይ ነው።

ሁለቱን ቁልፍ ሥልጣኖች ሺ የተረከቡት ባለፈው ጥቅምት ነበር። ሺ ያን ጊዜ ለሦስተኛ ዙር ፕሬዚዳንት እንደሚሆኑም የሚጠበቅ ነበር።

ከፕሬዚዳንት ሺ ቃለ መሐላ መፈጸምና ሦስተኛ ዘመን በፕሬዚዳንትነት ሥራ ከመጀመር ይልቅ አሁን ትኩረት የተሰጠው አዲስ ለሚሾሙ ሚኒስትሮች ማንነት ነው።

የፕሬዚዳንቱ ታማኝ ናቸው የሚባሉት ሊ ቺያንግ ከጥቂት ሰዓታት በፊት አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሰይመዋል።

ሊ ይህን ሥልጣን ከመቆናጠጣቸው በፊት በቻይና ትልቅ ከተማ ሻንጋይ የኮሚኒስት ፓርቲ መሪ ነበሩ። ሊ ቺያንግ 63 ዓመታቸው ነው።

ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ ማንም ጋዜጠኛ እንዲገባ ያልተፈቀደ ሲሆን በውጤቱም 2936 አባላት ድምጽ ሰጥተዋቸዋል። ተቃውሞም ሆነ ድምጽ ተአቅቦ አልተመዘገበም።

በዚህም መሠረት ሊ ቺያንግ በቻይና ሁለተኛው ቁልፍ ባለ ከፍተኛ ሥልጣን ይሆናሉ ማለት ነው። አዲስ የሚሾሙት ሌሎች ሚኒስትሮች ለሺ ጂንፒንግ ፍጹም ታማኝ የሆኑት ብቻ እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

ቤጂንግ ከዋሺንግተን ጋር በየጊዜው እየሻከረ የመጣው ግንኙነት በአዲሱ አስተዳደር ምን ሊመስል ይችላል የሚለውም ሌላው የፖለቲካ ተንታኞችን የሳበ ጉዳይ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቻይና ላከቻቸው የተባሉ የስለላ ፊኛዎች የሁለቱን ኃያል አገራት ግንኙነት በመጠኑ አበላሽቶታል።

ከማኦ ዜዶንግ ወዲህ በቻይና ፕሬዚዳንቶች ከሁለት ዘመን በላይ እንዳያገለግሉ ይደረግ ነበር።

ከአምስት ዓመታት በፊት ይህን ደንብ የሻሩት ሺ አሁን ለሦስተኛ ጊዜ በፕሬዚዳንትነት ለማገልገል ቃለ መሐላ ፈጽመዋል።

በተደረገው ጉባኤ የ68 ዓመቱ ሃን ዠንግ ምክትል ፕሬዚዳንት አድርጎ መርጧቸዋል። ዠንግ የፖሊት ቢሮ ቋሚ ኮሚቴ አባል ናቸው።



ሺ ጂንፒንግ

በቻይና ምክትል ፕሬዚዳንትና ሌሎች ሥልጣኖች በትክክል ኃላፊነታቸው በውል የሚታወቅ ባይሆንም የቀድሞው ምክትል ፕሬዚዳንት ዋንግ ኪሻን የጸረ ሙስና ዘመቻን የመሩ ሰው ናቸው።

## በሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ ተጠያቂ የነበረው ካቡጋ የፍርድ ሂደት በጊዜያዊነት ቆመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩዋንዳን የዘር ጭፍጨፋ በዋነኝነት አቀነባብረዋል የሚባሉት ፌሊሴ ካቡጋ በሄግ እየተካሄደ ያለው የፍርድ ሂደት በጊዜያዊነት ቆመ።

የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ይነዛ የነበረው አርቲኤልኤም (RTLM) ራዲዮ ጣቢያ ባለቤትም የ90 ዓመቱ ካቡጋ በሄግ የዓለም አቀፍ ወንጀል ፍርድ ቤት ሲዳኙ ቆጥቷል።

ጠበቆቻቸው የመርሳት ህመም ስላለበት ፍርድ ለመቅረብ ብቁ አይደለም ማለታቸውንም ተከትሎ ነው በጊዜያዊነት የቆመው።

ካቡጋ ከ26 ዓመታት ዓደን በኋላ ነው ከሶስት ዓመታት በፊት በቁጥጥር ስር የዋለው። የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ጤንነቱ እስኪገመገም የፍርድ ሂደቱ በጊዜያዊነት እንዲቆም ተስማምቷል።

ፈሊሴ ካቡጋ የኢንተርሃምዌይ ሚሊሻዎች የመንፈስ አባት ይሉታል። ያኔ የተገደሉት የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ጁቬናል ሃቢያሪማና የቅርብ ወዳጅም ነበር። ቤተሰብም ነበር፤ በጋብቻም ተሳስሯል።

በዚያ ዘመን እጅግ የናጠጠው የሩዋንዳ ዜጋም ፈሊሴ ካቡጋ ነበር። ሻይ ቅጠል ንግድ የእርሱን ያህል የነገደ አፍሪካዊ አልነበረም። ከፍተኛ ሃብትም አካብቷል።

የሁቱ ጨፍጫፊዎችን አስታጥቆ ያደራጀ፣ ለቱትሲዎች መጨፍጨፊያ ይሆን ዘንድ ካራ ከነመሞረጃው ወደ አገር ቤት በገፍ ያስገባው እርሱ ነበር ይባላል።

ፈሊሴ ካቡጋ በዘር ማጥፋት ወንጀል ከሚፈለጉት ሰዎች ቁጥር አንዱ ብቻም ሳይሆን አየሁት ለሚል 5 ሚሊዮን የሚያሸልም ውድ ወንጀለኛ ነበር።

ካቡጋ በሃሰተኛ ማንነት በፓሪስ ውስጥ በሚገኝ አፓርታማ ውስጥ ይኖር እንደነበር የደረሱበት የፈረንሳይ መርማሪዎች ናቸው። 28 የተለያዩ ማንነቶችና ስሞች ነበሩት።

ከዘር ጭፍጨፋው የተረፉ ሩዋንዳውያን ካቡጋ በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ሊሞት ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ገልጸዋል። የፍርድ ሂደቱ ዓመታትም እንደሚወስድ ይጠበቃል።



ፌሲሴ ካቡጋ


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

ኦሞ ባንክ አ.ማ ሶዶ ዲስትሪክት በአዋጅ ቁጥር 97/90 98/90 እና 592/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት በዋስትና የያዘውን ንብረት ባሉበት ሁኔታ በግልጽ ሐራጅ ይሸጣል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው ስም | የንብረት አስያዥ ብም | ለጨረታ የቀረበው መያዣ ንብረት | አበዳሪው ቅርንጫፍ | ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻና የቦታ ስፋት | | | | የጨረታ መነሻ ዋጋ | የጨረታው ቀንና ሰዓት | | ጨረው የወጣው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ከተማ/ ወረዳ | ቀበሌ | የካርታ ቁጥር | የቦታ ስፋት በካ.ሜ | | ቀን | ሰዓት | ለመጀሪያ ዙር/ጊዜ |
| 1 | ሰላም የወተት ላም ዕርባታ | አቶ ሃብታሙ በቀለ | መኖሪያ ቤት | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 01 | 81152/15/10 | 250 | 270,000 | 05/08/2015 | 3:00-4:00 | |
| 2 | መጋዘን የወተት ላም ዕርባታ | አቶ ኤልያስ ቶንጀ | መኖሪያ ቤት | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 02 | 924/10/09 | 200 | 210,000 | 05/08/2015 | 4:00-5:00 | |
| 3 | ካሃ የወተት ላም ዕርባታ | አቶ ባንጃው በራታ | መኖሪያ ቤት | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 02 | 3031/10 | 600 | 110,000 | 05/08/2015 | 5:00-6:00 | |
| 4 | ሳርሳ የወተት ላም ዕርባታ | አቶ ኢሳያስ መና | መኖሪያ ቤት | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 02 | 129628/10/06 | 360 | 350,000 | 05/08/2015 | 6:00-7:00 | |
| 5 | ወ/ሮ ምህረት ሳሙኤል | አቶ ዘውድነህ ታንጋ | መኖሪያ ቤት | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 02 | 128064/10/06 | 300 | 350,000 | 05/08/2015 | 7:30-8:30 | |
| 6 | ፋርስ አጠ/መጠጥ ማከፋፈያ | አቶ ታክስዮን ሌራ | ንግድ | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ፋርቾ ከተማ | 01 | 075 | 300 | 120,000 | 05/08/2015 | 8:30-9:30 | |
| 7 | ወ/ሮ መሰለች ጫንቆ | አቶ መሸሻ መስቀሌ | ንግድ | ኦሞ ባንክ ጠበላ ቅርንጫፍ | ጠበላ ከተማ | 02 | 129249 | 400 | 280,000 | 05/08/2015 | 10:00-11:00 | |

* ተጫራቾች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 10% የጨረታ ማስከበሪያ ቦንድ በባንክ ክፍያ ማዘዣ ሲ.ፒ.ኦ አሰርተው ከጨረታው ቀን በፊት ማስያዝ ወይም ጨረታው በሚካሄድበት ዕለት ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ይዘው መቅረብ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
* ጨረታው በሰንጠረዡ ላይ በተጠቀሰው ቀንና ስአት ባለዕዳዎቹ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ታዛቢዎች በተገኙበት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ለሃራጅ በወጣው መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት ይካሄዳል፡፡
* ጨረታውን ያሸነፈው ተጫራች ያሸነፈበትን ዋጋ በ15 ቀን ውስጥ ለባንክ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
*ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ገቢ የማያደርግ ተጨራች ጨረታው ተሰርዞ ያስያዘው ገንዘብም አይመለስለትም፡፡
* በባንኩ የብድር ፖሊሲ መሰረት የሚፈለገውን ማሰረጃ አሟልቶ ለቀረበ የጨረታ አሸናፊ ብድርን በተመለከተ ቀርበ የባንኩን የብድር ዳይሬክቶሬት ማነጋገር ይችላል።
* ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 046-212-52-17 ዋና መ/ቤት ወይም 046-180-21-06 ለሶዶ ዲስትሪክት ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡
* ንብረቱ በገዥው ስም እንዲዘዋወረ ባንኩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ድብዳቤ ይጽፋል፡፡
* ባንኩ የተሻል አማረጭ ካገኘ ብድሩ ከተከፈለ ጨረታውን የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
* ጨረታውን ያሸነፈ ተጫራች ለመንግስት የሚከፈለውን አስፈላጊ ብር፤ ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ለመንግስት የሚከፈለውን ማንኛውንም ውዝፍ ክፍያ ይከፍላል፡፡

**ኦሞ ባንክ ሶዶ ዲስትሪክት**

# ስፖርት





## ስፖርት በስደተኞች ህይወት

**ብርሃን ፈይሳ**

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት ብቻ ከዓለም ህዝብ 103 ሚሊየን የሚሆኑት ቤት ንብረታቸውን ጥለው ለስደት ተዳርገዋል:: ታዲያ ከእነዚህ ስደተኞች መካከል 72 ከመቶ የሚሆኑት የሶሪያ፣ ቬንዙዌላ፣ ዩክሬን፣ አፍጋኒስታን እና ደቡብ ሱዳን ዜጎች ናቸው:: ስደትን አስከፊ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል ማሳያ የሚሆነው ደግሞ እአአ በ2021 ለስደት ከተዳረጉ ሰዎች መካከል 41 ከመቶ የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶችና ህጻናት መሆናቸውን የዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት መረጃ ያሳያል::

በተለያዩ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች የተነሳ ለስደት የሚዳረጉት እነዚህን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎችም የተለያዩ ተቋማት በሚያዘጋጁት የስደተኛ ጣቢያዎች እገዛ ይደረግላቸዋል:: ከመሰረታዊ ድጋፍ ባለፈ ስደተኞች ካሳለፏቸው ከባድ ሁኔታዎች እንዲያገግሙና ወደ መልካም ማህበረሰባዊ ግንኙነት እንዲመለሱ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ:: ከእነዚህ መካከል አንዱ ስፖርት ሲሆን፤ አእምሯዊና አካላዊ ጤንነታቸውን ለመጠበቅም መሰረታዊ መሳሪያ ነው:: ስፖርት ማህበረሰብን በማንቃት፣ ንቅናቄን በመፍጠር፣ ጎጂ ልማዶችን በመቅረፍ፣ መልካም እሳቤን በማስረጽ እንዲሁም የእርስ በእርስ ግንኙነትን በማዳበር ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑ፤ እንደ ተባበሩት መንግስታት ያሉ ተቋማት በስፋት ይንቀሳቀሱበታል::

አሁን የ24 ዓመት ወጣት የሆነው አራም ማህሙድ በሶሪያ ደማስቆ ነበር ተወልዶ ያደገው:: ነገር ግን በአገሩ በተነሳው ጦርነት ምክንያት ከዓመታት በፊት ወደ ኔዘርላንድ ሊሰደድ የግድ ሆነ:: በአገሩ ሳለ የባድሜንተን ስፖርትን የሚያዘወትረው ይህ ወጣት ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መድረሻውን ባደረገበት የስደተኞች ካምፕ ዳግም





በቶኪዮ ኦሊምፒክ ተሳታፊ የነበረው የስደተኞች ኦሊምፒክ ቡድን፤

የሚወደውን ስፖርት መከወን ቻለ:: በስፖርቱ ምክንያትም ያሳለፈውን መከራ ከመርሳት አልፎ አዳዲስ ጓደኞችን ማፍራትና ሌሎች ቋንቋዎችንም ለማወቅ ችሏል:: በዚህም ‹‹ስፖርት እጅግ ረድቶኛል›› ሲል ይናገራል::

በእርግጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ብቻውን ዓላማቸውን ከግቡ ማድረስ አይችልም፤ በመሆኑም ተቋማቱ ከዓለም አቀፍ የስፖርት ማህበራት ጋር በጥምረት ይሰራሉ:: ከእነዚህ መካከል አንዱ የሰው ልጆችን በጎ እንቅስቃሴ የሚዳስሰውና ሁሌም ከተገፉት ጎን በመቆም የሚታወቀው ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ነው:: ኮሚቴው ለረጅም ዓመታት ከእነዚህ ተቋማት ጋር በተለያየ መልክ ሲሰራ ከቆየ በኋላም እአአ ከ2016 አንስቶ የስደተኞች ስፖርትን በሚመለከት መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ ችሏል:: ይኸውም የስደተኞች ስፖርት ቡድንን በማቋቋምና ኮሚቴውን እንዲወክሉ በማድረግ በብራዚሉ የሪዮ ዴጄኔሮ ኦሊምፒክ እና ፓራሊምፒክ እንደማንኛውም ቡድን በማሳተፍ ነው:: በመክፈቻው ወቅትም ስፖርተኞቹ በኮሚቴው ባንዲራ እና መዝሙር ታጅበው ከአዘጋጅ አገር ቀጥሎ ነበር ወደ ትርኢት ማሳያው ስታዲየም ያቀኑት:: እአአ በ2020ው የቶኪዮ ኦሊምፒክም በተመሳሳይ ቡድኑ ለሁለተኛ ጊዜ ተካፋይ ሆኖ ነበር:: ይህም በስፖርት ተሰጥኦና ብቃት ላላቸው ስደተኞች ተስፋ ሊሆናቸው ችሏል::

በሪዮ ኦሊምፒክ አስር ስፖርተኞች በአትሌቲክስ፣ ውሃ ዋና እና ጁዶ ሲሳተፉ፤ በቶኪዮ ደግሞ 29 ተወዳዳሪዎች በአትሌቲክስ፣ ውሃ ዋና፣ ብስክሌት፣ ቦክስ፣ ባድሜንተን፣ ቀዘፋ፣ ጁዶ፣ ካራቴ፣ ቴኳንዶ፣ ክብደት ማንሳት፣ ትግል እና በኢላማ ተኩስ ተካፍለዋል:: በኦሊምፒኩ ላይ ተሳታፊ ከሆኑት የሚልቁ ስደተኛ ስፖርተኞች ደግሞ በተለያየ መልክ ድጋፍ እና እገዛ በኮሚቴው ተደርጎላቸዋል::

መሃሙድም የዚሁ እድል ተጠቃሚ በመሆኑ ዛሬ ላይ ህይወቱ ሊለወጥ ችሏል:: በስደተኛ ጣቢያው ባድሜንተንን ከማዘውተር አልፎ ክለቦችን እስከ መቀላቀልና በውድድሮችም እስከመሳተፍ ደርሷል:: በሂደትም ዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ በቶኪዮ ኦሊምፒክ ቡድን ተመርጦ በታላቁ መድረክ ራሱን አግኝቷል:: በመጨረሻም የልጅነት ህልሙ ስለተሳካለት ‹‹በህይወት ዘመኔ የማልረሳው፣ ማንም የማይነጥቀኝ ትውስታዬ ነው›› ሲል ስፖርት ያስገኘለትን እድል ይገልጻል::

ይህንን የተመለከቱ ሌሎች ዓለም አቀፍ የስፖርት ማህበራትም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በሚያካሂዷቸው ቻምፒዮናዎች ላይ የስደተኞች ቡድንን ማካተት ጀምረዋል:: እርምጃውን ከወሰዱ ማህበራት መካከል አንዱ የዓለም አትሌቲክስ ሲሆን፤ እአአ በ2017 በተካሄደው የዶሃ ዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለስደተኞች የተሳትፎ እድል ሰጥቷል:: በዚህ ያላበቃው ማህበሩ ከቻምፒዮናው በኋላም ድጋፉን አጠናክሮ በመቀጠል ለሙከራ የሚሆኑ የስልጠና ፕሮጀክቶችንም መክፈት ችሏል:: የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት የሚመራው ፊፋም በተመሳሳይ በስደተኞች ጉዳይ ላይ ከግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር የሚሰራ ራሱን የቻለ ድርጅት አቋቁሟል:: በዚህም በ78 አገራት ላይ የሚሰሩ 169 ግብረሰናይ ድርጅቶች በተለይ በህጻናት ስፖርት ላይ አተኩረው እንዲሰሩ ይረዳል::

የወርልድ ቴኳንዶ እና የጁዶ ፌዴሬሽኖችም በሚመሯቸው ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ስደተኛ ቡድኑን ያሳትፋሉ::





## ልጆች ስለወፎች ምን ታውቃላችሁ?

**ሰላማዊት ውቤ**

ሰላም ልጆች እንደምን አላችሁ ! ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? ለሁለተኛ ሴሚስተር ፈተና ዝግጅት ማድረግ የሚቻለው በዕየለቱ የምትማሩትን ትምህርት ከሥር ከሥር በማጥናት እንደሆነ ታውቃላችሁ አይደል? ይሄን ካወቃችሁ በጣም ጎበዞች ናችሁ:: ግን ደግሞ ከጥናት ጎን ለጎን ባለ ትርፍ ጊዚያችሁ ስለ ሌሎች ከትምህርታችሁ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያያዙ ብዙ ነገሮችንም ማወቅ ይገባችኋል::

ለምሳሌ የእንስሳት መዘክሮች ወይም ሙዚየሞች ብትጎበኙ ጥሩ ትምህርት ታገኛላችሁ:: ክፍል ውስጥ የተማራችሁትን ትምህርትም በተግባር ለማረጋገጥ የሚያስችል ዕውቀት ትቀስማላችሁ:: ልጆች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የእንስሳት የተፈጥሮ ቅርስ መዘክርን ስንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ?

በመዘክሩ ውስጥ የተለያዩ እንስሳቶች ይገኛሉ:: ከእነዚህ መካከል የተለያዩ የወፍ ዝርያዎች ይጠቀሳሉ:: ለዛሬ እኛም መዘክሩን ላልጎበኛችሁት ልጆች ስለእነዚህ የወፍ ዝርያዎች ልንነግራችሁ ወደናል:: አስጎብኛችን ወይዘሮ አምሳለ ተፈራ ይባላሉ:: እርሳቸው እንደነገሩን ይሄ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የእንስሳት የተፈጥሮ ቅርስ መዘክር በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው መዘክር (ሙዚየም) ነው:: ከተመሰረተ ዘንድሮ 54ኛ ዓመቱን ይዟል::

ቀደም ሲል ሥፍራው የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር እንጂ የሙዚየም አልነበረም:: ከጥናትና ምርምሩ ዝግጅት በኋላ በቀጣይ ምን ይሁን በሚል ምክክር ተደርጎ ነው ለእንስሳት መዘክርነት እንዲውል የተወሰነው:: ታዲያ በቀን ከስድስት ሺህ ተማሪዎች በላይ ያስተናግዳል:: ለጉብኝት ከሚመጡት ተማሪዎች በአብዛኛው በክፍል ውስጥ የተማሩትን በተግባር ለማረጋገጥ የሚመጡ ናቸው::



ፎቶ- አዩብ ተፈራ

የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ወደ መዘክሩ ለጉብኝት ከመምጣታቸው በፊት በደብዳቤ ፕሮግራም ያሲዛሉ:: የመግቢያ ዋጋው ለተማሪ አምስት ብር ለአዋቂዎች ደግሞ 15 ብር ነው:: አገር ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የውጭ ዜጋ ጎብኚዎች ደግሞ 50 ብር ይከፍላሉ:: መዘክሩ የአውድ ዓመት በዓላትን ጨምሮ ከእሁድ እስከ እሁድ ለጉብኝት ክፍት ነው::

እኛ እንደጎበኘነው ታዲያ በመዘክሩ የተለያዩ እንስሳቶች በስድስት ክፍሎች ተከፋፍለው ለጉብኝት ቀርበዋል:: አስጎብኛችን እንደነገሩን አምስተኛውና ስድስተኛው ክፍል የተለያዩ የወፍ ዝርያዎች የሚገኙበት ነው:: የወፍ ዝርያዎቹ በዚህ ክፍል ውስጥ ብቻ ያሉት አይደሉም:: ገና ያልተሰበሰቡና ወደ ክፍሉ ያልመጡ ብዙ የወፍ ዝርያዎች አሉ:: ታዲያ በራሪዎቹ የወፍ ዝርያዎች በሙሉ በመጠን አነስ ያሉ ናቸው:: ከእነዚህ ወፎች ውስጥ ሁሌ በአካባቢያችሁ ሲበሩ የምታይዋቸው ወፎችና እርግቦች ይገኙበታል::

እነዚህ ወፎች ጥራጥሬ ነው የሚመገቡት:: ቢሆንም መሬት ላይ ያገኙትን ነገር ሁሉ እየለቀሙ ወደ ጎጇቸው ይወስዳሉ:: በተለይ አኘከን የተፉነውን ማስቲካም የሚወጡበት ጊዜ ቀላለል አይደለም:: ነገር ግን ማስቲካው ጉሮሯቸው ላይ ስለሚለጠፍ ተሰቃይተው ይሞታሉ:: ስለዚህ አስጎብኛችን ማስቲካ አኝከን ከመትፋታችን በፊት በወረቀት ጠቅልለን መጣልና ወፎቹን ከስቃይና ሞት መታደግ እንዳለብን ነግረውናል::

በመዘክሩ ውስጥ ውሃ ውስጥና ውሀ አካባቢ የሚገኙም የወፍ ዝርያዎችም አሉ:: ወፎቹ በሙሉ ዋናተኛ ናቸው:: እንደ ዳክየና ዝይ ያሉ ዋናተኞቹ ወፎች እግሮቻቸው አንድ ላይ የተያያዙና የተጣበቁ ሲሆኑ፤ ሥጋ በል የሆኑ ወፎችም በክፍሉ ውስጥ አሉ:: ስጋ በሎቹ ወፎች አፋቸው ወይም መንቁራቸው በጣም የሾለና የታጠፈ ነው:: የሚመገቡትን እንስሳ ወግተው ለመግደልም የሚያስችሏቸው ሹል ጥፍሮቻቸውና ጠንካራ አፎቻቸው ናቸው:: ልጆች ንስር የሚባለውም ከእነዚሁ የወፍ ዝርያዎች ይካተታል:: ንስሮች በአብዛኛው የሞተ እንስሳ አይበሉም:: በሕይወት ያለ እንስሳ በማደን ራሳቸው ገድለው ነው የሚመገቡት:: ከርቀትም እስከ አምስት ኪሎ ሜትር ወደ ታች መውረድና መብረር እንዲሁም ከፍታ ላይ መብረር ይችላሉ::

ሴክረተሪ በርድ የሚባሉም የወፍ ዝርያዎች አሉ:: የስማቸው መነሻ ላባቸው ሲሆን፤ በድሮ ጊዜ ቀለም ተነክሮ ይጻፍበት ስለነበረ ከጸሐፊነት ጋር ተያይዞ የወጣላቸው ነው ይባላል:: ሌላው ምክንያት አፈጣጠራቸው በዓይን ሲታዩ አጭር የለበሱ፤ የተኳኳሉና ጫማ የለበሱ መምሰላቸው ነው:: ሴክረተሪ በርዶች ሥጋ በል የወፍ ዝርያ ናቸውም::

ሌላው በመዘክሩ ውስጥ ያለው ቅልጥም ሰባሪ የሚባል የወፍ ዝርያ ሲሆን፤ ይሄ ወፍ አጥንት ወይም ቅልጥም ይዞ በጣም ወደ ላይ ከፍ ብሎ እየበረረ ይሄድና ትልልቅ ድንጋይ ፈልጎ አጥንቱን ወደ ታች ይለቀዋል:: አጥንቱ ሲሰበር ከከፍታ ወደ ታች ወደ መሬት ይወርድና ከውስጡ ያለውን መቅኒ ወይም ቅባትና የአጥንት ስብርባሪ ይመገባል:: በዚህም መገኛው ብዙ ጊዜ ተራራማ ቦታዎች ላይ ነው::

ልጆች አሁን ስድስተኛው ክፍል ውስጥ ስንገኝ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት የወፍ ዝርያዎች ጥንብ አንሳ የሚባሉት አይነት ናቸው:: በአብዛኛው የሚመገቡት የሞተ እንስሳትን ነው:: በዚህ ትይዩ በአብያታ ሐይቅ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ወፎች ይገኛሉ::

ጥሬም ሥጋም የሚበሉ የወፍ ዝርያዎች በዚህ ክፍል ውስጥ አሉ:: ከእነዚህም ወፎች መካከል ቆቅና ጅግራ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው:: ወፎቹ ቀለማቸው ይለይ እንጂ ቅርጻቸው ዶሮ ይመስላል:: ሥጋቸውም እንደ ዶሮ ሁሉ ይበላል:: አብራቸው ጉጉት የምትባል የወፍ ዝርያ ትገኛለች:: ጉጉት በአብዛኛው ማታ ማታ ታድናለች:: በአብዛኛው ዓይናቸው የሚያየውም በማታ ብቻ ነው::

እርኩም እንዲሁም አሞራ ወይም ቁራ ብለን የምንጠራቸውና ዝርያቸው ከወፍ የሚመደብ የወፍ ዝርያዎችም ሌሎቹ በስድስተኛው ክፍል የሚገኙ ናቸው:: ወፎቹ ሥጋም ጥሬም ይመገባሉ:: ቁራዎቹ አንገታቸው ላይ ነጭ አለባቸው:: የቁጥቋጦ ቁራ የምትባልም አለች:: ይህች ቁራና በቀቀን ከተሰኙት የወፍ ዝርያዎች ውስጥ ግንባረ ቢጫ በቀቀኖች በተጨማሪም ሰማያዊ ክንፍ ዝይን ወፎች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ ዝርያዎች ናቸው:: ስለዚህ ሄዳችሁ ጎብኙ በማለት ለዛሬ አበቃን:: መልካም ሰንበት !!